LIVING GOSPEL CHURCH

ሕያው ወንጌል ቤተ ክርስቲያን

# የ1ኛ እና 2ኛ ጴጥሮስ መልዕክት ጥናት

## በዊንፔግ ካናዳ ሕያው ወንጌል ቤተክርስትያን የተዘጋጀ

## የመጽሃፍ ቅዱስ ጥናት

አድራሻ፡ 525 William Avenue Winnipeg, MB

መግቢያ ..... 3
ታሪካዊ ዳራ ..... 3
ጴጥሮስ መልዕክቱን የጻፈው ለማን መቼ እና የት ተጻፈ? ..... 6
አንደኛ ጴጥሮስ የተጻፈበት ጊዜና ስፍራ..... 7
የ1ኛ ጴጥሮስ መልዕክት ዓላማ፣ ባሕሪያት፣ መዋቅር እና አስተዋጽኦ ..... 8
የ1ኛ ጴጥሮስ መልዕክት ልዩ ባሕርያት ..... 9
የ1ኛ ጴጥሮስ መልዕክት መዋቅር..... 9
የ1ኛ ጴጥሮስ መልእክት አስተዋጽኦ ..... 10
ጥናት አንድ፡ የክብር ተስፋ..... 11
ከስደት ባሻገር ድነታችን (ደኅንነታችን) ትልቅ ሽልማት ያስገኝልናል..... 11
የንባብ ክፍል፡ 1ኛ ጴጥሮስ 1፡1-12 ..... 11
➢ ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን? ..... 13
ጥናት ሁለት፡ ቅድስና..... 14
የንባብ ክፍል (1ኛ ጴጥ. 1፡13-2፡3) ..... 14
ጥናት ሦስት፡ የንጉስ ካህናት ..... 16
የንባብ ክፍል (1ኛ ጴጥ 2፥4-12) ..... 16
ጥናት አራት፡ ክርስትያናዊ ምሳሌነት ..... 18
የንባብ ክፍል፡ (1ኛ ጴጥ 2፥13-25) ..... 18
➢ ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን? ..... 19
ጥናት አምስት፡ ክርስትና እና መከራ..... 20
የንባብ ክፍል፡ (1ኛ ጴጥ 3፥1-22) ..... 20
➢ ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን? ..... 22
ጥናት ስድስት፡ የተቀደሰ ሕይወት መምራት ..... 23
የንባብ ክፍል፡ (1ኛ ጴጥ 4፥1-19) ..... 23
➢ ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን? ..... 23
ጥናት ሰባት፡ መልካም ምክር ..... 27
የንባብ ክፍል፡ (1ኛ ጴጥ. 5፡1-14) ..... 25
➢ ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን? ..... 27
የ2ኛ ጴጥሮስ ..... 28
መግቢያ ..... 28
የ2ኛ ጴጥሮስ ጸሐፊ..... 28
ጴጥሮስ መልእክቱን የጻፈው ለማን ነው?..... 28

2ኛ ጴጥሮስ የተጻፈበት ጊዜና ቦታ ..... 29
የ2ኛ ጴጥሮስ ልዩ ባሕርያት ..... 30
የ2ኛ ጴጥሮስ መዋቅር ..... 30
የ2ኛ ጴጥሮስ አስተዋጽኦ ..... 30
ጥናት አንድ፡ መመረጥና መጠራትን ማወቅ ..... 32
የንባብ ክፍል፡ (2ኛ ጴጥ 1፥1-11) ..... 32
➢ ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን? ..... 32
ጥናት ሁለት፡ የቅዱሳት መጽሃፍት ትንቢትን መመርመር ..... 34
የንባብ ክፍል፡ (2ኛ ጴጥ 1፥12-21) ..... 34
➢ ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን? ..... 34
ጥናት ሶስት፡ ሐሰተኛ ነብያትና አደገኛነታቸው ..... 36
➢ ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን? ..... 36
ጥናት አራት፡ የጌታን መምጣት መጠባበቅ ..... 38
➢ ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን? ..... 38
ዋቤ መጽሃፍት፡ ..... 40
ድህረገጾች፡ ..... 40

## መግቢያ

### ታሪካዊ ዳራ

የአንደኛ ጴጥሮስ መልዕክት ጥንታዊ የደብዳቤ አጻጻፍ ስልት በመከተል የጸሐፊውን ማንነት በማስተዋወቅ ይጀምራል። እርሱም ጴጥሮስ መሆኑን ይነግረናል። ጴጥሮስ ልክ እንደ ጳውሎስ ራሱን ሐዋርያ ብሎ ይጠራዋል። ይህን ያደረገው በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ሌሎች ጴጥሮስ ተብለው የሚጠሩ ሰዎች ስለነበሩ፥ የመልእክቱ ጸሐፊ ማን እንደሆነ ለይቶ ለማሳወቅ ብቻ ሳይሆን፥ ከዚህ በበለጠ ግን መልእክቱን ለመጻፍ ምን ሥልጣንና ስፍራ እንዳለው ለሕዝቡ ለማሳወቅ ይፈልጋል። መልእክቱን የሚጽፈው እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ነው።

ሐዋርያው ጴጥሮስ ምናልባትም በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ የታወቀ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሳይሆን አይቀርም። የጴጥሮስ አይሁዳዊ ስሙ ስምዖን ሲሆን፥ በገሊላ የተወለደ አይሁዳዊ ነበር። ይህች ስፍራ በፓለስታይን ምድር ውስጥ ብዙም ያላደገች ነበረች። በገሊላ አካባቢ አይሁዶችም አሕዛብም ይኖሩ ነበር። ጴጥሮስ ያደገው ምናልባትም የግሪክና የአረማይክ ቋንቋዎችን እየተናገረ ይሆናል። አባቱ ዓሣ አጥማጅ ነበር። ከዚህም የተነሣ ከወንድሙ እንድርያስ ጋር ዓሣ አጥማጆች ሆኑ። የጴጥሮስ መንፈሳዊ እድገት የጀመረው መጥምቁ ዮሐንስን ባገኘው ጊዜ ሳይሆን አይቀርም። ወንድሙ እንድርያስ የመጥምቁ ዮሐንስ ተከታይ ስለነበር፥ ጴጥሮስም እንዲሁ የዮሐንስ ደቀ መዝሙር የነበረ ይመስላል (ዮሐ 1፥40-42)

ክርስቶስ ከተጠመቀ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ እንድርያስ ጴጥሮስን ከክርስቶስ ጋር አስተዋወቀው። ከዚያም በኋላ ጴጥሮስ ቀሪ ዘመኑን ሁሉ ክርስቶስን ይከተልና ያገለግል ጀመር። ክርስቶስ መጀመሪያ አገልግሎቱን በገሊላ በጀመረ ጊዜ ጴጥሮስ አብሮት ጥቂት ጊዜ ካሳለፈ በኋላ (ዮሐ. 2) ቤተሰቡ ወደሚተዳደርበት ዓሣ የማጥመድ ተግባር የተመለሰ ይመስላል። ኢየሱስ ይፋዊ አገልግሎቱን በጀመረ ጊዜ፥ ካከናወናቸው ተግባራት አንዱ ጴጥሮስ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ እንዲሆን መጥራት ነበር። ጴጥሮስ አንድ ቀን በዓለም ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያሰራጭ ተማሪ ነበር (ማቴ 4፥18-20)

ሦስት ዓመት ተኩል ጴጥሮስ ከኢየሱስ ጋር በመሆን ተአምራቱን ሲመለከት፥ ስብከቶቹን ሲሰማና በክርስቶስ ለአገልግሎት ሲላክ እንመለከታለን። በዚህም አገልግሎቱ ተአምራትን የማድረግና በእሥራኤል ምድር ሁሉ ለመስበክ ተልኮአል። ጴጥሮስ የመሪነት፥ የድፍረትና የችኩልነት ባሕርያት ያሉት ይመስላል። ክርስቶስ ጴጥሮስን ከብዙ ተከታዮቹ መካከል ለይቶ ብዙ ጊዜውን አብሯቸው ከሚያጠፋው ከ12ቱ ደቀ መዛሙርቱ ውስጥ አካተተው። በተጨማሪም፥ ክርስቶስ ለወደፊት የቤተ ክርስቲያን መሪነት ይጠቅሙ ዘንድ ተጨማሪ ጊዜ ወሰደ። ከሚያሠለጥናቸው ሦስት ደቀ መዛሙርት (ከያዕቆብና ዮሐንስ ጋር) አንዱ ጴጥሮስ ነበር።

ጴጥሮስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ መሢሕ እንደሆነ በድፍረት ባወጀ ጊዜ (ማቴ 16፥16-20)፥ ክርስቶስ ስሙን ከስምዖን ወደ ኬፋ (አረማይክ) ወይም ጴጥሮስ (ግሪክ) ለወጠው። ይህም ዓለት የሚል ፍቺ ይሰጣል። ይህ የስም ለውጥ ለጴጥሮስ የሚሰጠውን ልዩ ኃላፊነት እና ሥልጣን ያመለክታል። ጴጥሮስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን የሚመሠርትበት ዓለት ይሆን ነበር። ብዙም ሳይቆይ ግን የጴጥሮስ ድፍረትና እምነት ግን ይከስማል። ክርስቶስ ከመሰቀሉ በፊት በአይሁድ አለቆች በሚመረመርበት ወቅት፥ ጴጥሮስ ኢየሱስን ሦስት ጊዜ ካደው። ጴጥሮስ በዚያን ሌሊት ክርስቶስን መካዱን በፍጹም ሊረሳው አልቻለም። በአንደኛ ጴጥሮስ ውስጥ እንኳን ሳይቀር ስለዚሁ ጉዳይ ይጠቅሳል። ሥቃይ ልቡን እየናጠው ጴጥሮስ በምሬት አለቀሰ። ከትንሣኤ በኋላ ግን፥ ኢየሱስ ፍቅሩንና ይቅርታውን በሚያሳይ መልኩ ጴጥሮስን አነጋገረው። በዚህም ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ዋና መሪ ወደ መሆኑ ኃላፊነት እንደገና መልሶ አስቀመጠው።

ጴጥሮስ በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዋና መሪ መሆኑ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የመጀመሪያዎቹ ገጾች ውስጥ ተመልክቷል። መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ በወረደ ጊዜ፥ የመጀመሪያውን ስብከት ያቀረበውና አይሁዶች በኢየሱስ አምነው የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንዲቀበሉ የጋበዛቸው ጴጥሮስ ነበር (የሐዋ. 2)። እግዚአብሔር ጴጥሮስ ለማኙን የመፈወስ የመጀመሪያውን ተአምር እንዲሠራ ተጠቅሞበታል (የሐዋ. 3)። ለእምነቱ በቀዳሚነት ስደትንና መከራን የተቀበለው ጴጥሮስ ነው። ወደ በኋላም ጴጥሮስ በዚሁ ርእሰ ጉዳይ ላይ ጽፎአል (የሐዋ. 4)። የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ለሰማርያውያን ወንጌልን በሰበከች ጊዜ የሰማርያውያንን እምነት እንዲገመግሙና ለሰማርያውያን አማኞች ሁሉ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንዲያስተላልፉ ቤተ ክርስቲያን ጴጥሮስና ዮሐንስን ነበር የላከቻቸው (የሐዋ 8፥14-17)። (ሰማርያውያን ከፊል አይሁዶችን ከፊል አሕዛብ ነበሩ።) እግዚአብሔር አሕዛብን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያመጣበት ጊዜ ሲደርስ፥ ጴጥሮስ ከቆርኔሌዎስ ጋር እንዲገናኝ አደረገ። ጴጥሮስ እየመሰከረ ሳለ መንፈስ ቅዱስ በመጀመሪያዎቹ አሕዛብ አማኞች ላይ ወረደ (የሐዋ. 10)። አሕዛብ ተጠምቀው ወደ አይሁዳዊነት ሳይለወጡ መንፈስ ቅዱስን ከእግዚአብሔር መቀበላቸው የጴጥሮስን አስተሳሰብ ለወጠው። በመሆኑም ወደ በኋላ ጴጥሮስ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያምኑትን አሕዛብ እንደሚቀበል አጥብቆ ሲከራከር እንመለከታለን (የሐዋ 15፥7-11)።

እግዚአብሔር ወንጌልን ወደ አሕዛብ ሁሉ ለማድረስ ጳውሎስ የተባለ ሌላ ሰው አስነሣ። ለጊዜው የአይሁዶች ሐዋርያ የተባለው ጴጥሮስ (ገላ 2፥8) በኢየሩሳሌም ተቀምጦ በፍልስጥኤም ምድር ላሉ አይሁዶች ሁሉ ሲሰብክ ኖረ። ጴጥሮስ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ የሚያገለግል ሰባኪ በመሆኑ ምክንያት ይመስላል፥ በኢየሩሳሌም የነበረችው የእናት ቤተ ክርስቲያን አመራር የክርስቶስ ወንድም ለነበረው ለያዕቆብ ተሰጠ (ገላ 1፥19)። ኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ከተጠናከረበት ጊዜ በኋላ፥ ጴጥሮስ በምሥራቃዊ የሮም ግዛት ውስጥ እየተዘዋወረ የወንጌል መልእክተኝነት አገልግሎት ይሰጥ እንደነበር ያሳያል። ጴጥሮስ በጳንጦስና በገላትያ፥

በቀጰዶቅያም፥ በእስያም፥ በቢታንያ ለተበተኑ መጻተኞች መልእክት ለማስተላለፍ በመፈለጉ ምናልባትም በእነዚህ አካባቢዎች ወንጌልን እንደ ሰበከ ሊያመለክት ይችላል። ጴጥሮስ የኋላ ኋላ ወደ ሮም እንደ ሄደ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያመለክታል። በዚያ ምን ያህል ጊዜ እንደ ሠራ አልተጠቀሰም። አንዳንድ ምሁራን ጳውሎስ በሮም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩትን አንዳንድ ክፍፍሎች ለማስተካከል ጴጥሮስን ጋብዞት ነበር ይላሉ። ነገር ግን በኔሮ ዘመነ መንግሥት ክርስቲያኖች ላይ ስደት በተነሣ ጊዜ ጴጥሮስ በምርኮኛነት ተወሰደ። አንድ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያሳየው፥ ሮማውያን ጴጥሮስን ለመግደል በመጡ ጊዜ እንደ ጌታ ኢየሱስ ለመሰቀል ባለመፈለጉ፥ ራሴን ዘቅዝቃችሁ ስቀሉኝ ብሏል። ይህ እውነት ይሁን እውነት አይሁን የሚታወቅ ነገር የለም። ምናልባትም ጴጥሮስ የሞተው ጳውሎስ በሞተበት ጊዜ አካባቢ ሳይሆን አይቀርም። ይህም በ67 ዓመተ ምሕረት አካባቢ መሆኑ ነው።

የአንደኛ ጴጥሮስ መልእክት የተጻፈው በጴጥሮስ ነው። ጴጥሮስ ይህንን መልእክት የጻፈው በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ ነው። ይህ መልእክት የተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ ከፍተኛ ጥራት ስላለው ምናልባትም መልእክቱን የጻፈው ስልዋኖስ (ሲላስ) ሳይሆን አይቀርም። ሲላስ ግሪክን በሚገባ ያውቅ የነበረ ሲሆን፥ ጴጥሮስ የሚናገረውን አሳብ በዚሁ መልእክት ውስጥ ሳያሰፍር አልቀረም። ጴጥሮስ በእርጅናው ዘመን ይህን መልእክት ሲጽፍ ከክርስቶስ ጋር ለረጅም ጊዜ የኖረ በመሆኑ መከራን መቀበል ምን እንደሆነ ያውቅ ነበር። በወጣትነቱ ጊዜ እርሱ እንዳደረገው ክርስቶስን እንዳይክዱና በመከራ ታግሰው እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን ሽልማት እንዲቀበሉ ያበረታታቸዋል።

የ1ኛ ጴጥሮስን መልእክት ልዩ የሚያደርጉ አምስት ገጽታዎች:

1. እንደ ዕብራውያን መልእክትና እንደ ዮሐንስ ራእይ ሁሉ መልእክቱ የሚያተኩረው ስለ ክርስቶስ ብለው በመከራ ስለሚያልፉ አማኞች መሆኑ
2. አማኞች ስለ ክርስቶስ ኢፍትሓዊ ስቃይ ውስጥ ሲያልፉ እንዴት መቋቋም እንዳለባቸው ትምህርት መስጠቱ
3. ክርስቲያኖች በዚህ ምድር እንግዶችና መጻተኞች መሆናቸውን ማውሳቱ
4. በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የተሰጡ መጠሪያዎችን በአዲስ ኪዳን መጠቀሙ እና
5. በአዲስ ኪዳን ለትርጓሜ አስቸጋሪ ምንባቦች ውስጥ 'በወህኒ ቤት ለነበሩት ነፍሳት ሰበከላቸው" በኖኅ ዘመን (1ኛ ጴጥ3፥19-20) የሚለውን ክፍል የያዘ መሆኑ ይህም ጌታ ኢየሱስ መቼ የት እንዴት እንደሰበከላቸው መረዳት አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱ ናቸው ።

በመጨረሻም በዚያ ዘመን ምንም እንኳን ክርስቲያኖች ለጥቂት ጊዜ በልዩ ልዩ ፈተና ቢያዝኑም በእነርሱ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁዋቸውም ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጁ እንዲሆኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት እንዲያደርጉት እየመከረ በዚህ ዘመን ለእኛ የመከራው ዓይነት ቢለያይም የልቡናችንን

ወገብ ታጥቀን በመጠን ኖረን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የምናገኘውን ጸጋ ፈጽመን ተስፋ በማድረግ በመከራ እንድንጸና ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሳይቀር እየጠቀሰ ጽፎልናል ።
ከላይ እንዳየነው የአንደኛ ጴጥሮስ መጽሐፍ የተጻፈው መከራ ለሚቀበሉ ክርስቲያኖች ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናቸው ምክንያት ሥራቸውን የማጣት፥ ከማኅበረሰቡ የመገለል፥ መሳለቂያ የመሆን፥ የመታሰርና የመደብደብ አደጋዎች ደርሰውባቸው ነበር። በመሆኑም፥ «ለሥቃይ የሚያጋልጠኝ ሆኖ ሳለ ክርስቶስን መከተሉ ተገቢ ነውን?» እያሉ ራሳቸውን ይጠይቁ ነበር። የአንደኛ ጴጥሮስ መልእክት ጸሐፊ ለእነዚህ አማኞች ለክርስቶስ መሠቃየት ክብር እንደሆነና የእግዚአብሔር ጥሪ አካል እንደሆነ ይገልጽላቸዋል። መከራን በምንቀበልበት ጊዜ፥ ለጽድቅ መከራ የተቀበለውን የክርስቶስን ሕይወት እንደግማለን። ምንም እንኳን ዲሞክራሲ ከስደት የምንላቀቅበትን ሁኔት ባመቻቸበት በዛሬው ዓለም ውስጥ ስለዚሁ ርእሰ ጉዳይ መነጋገሩ የሚያስደስተን ቢሆንም፥ የአዲሱ ትውልድ አማኞች ለእምነታቸው መሰደድ የእግዚአብሔር ፈቃድ አካል መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸዋል። አንድ ቀን ስደት ይመጣል፥ በመሆኑም እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ምላሽ እንሰጠው ዘንድ መዘጋጀት ይኖርብናል።

**ጴጥሮስ መልዕክቱን የጻፈው ለማን መቼ እና የት ተጻፈ?**

ጴጥሮስ በመግቢያው ላይ፥ «ለጳንጦስና፥ ለገላትያ፥ በቀጰዶቂያም፥ በእስያም፥ በቢታንያም ለተበተኑት መጻተኞች» ይላል። እነዚህ አውራጃዎች የሚገኙት ከትንሹ እስያ (የአሁኗ ቱርክ) በስተ ሰሜን ነበር። መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ እነዚህ አካባቢዎች እንዳይገባ ነግሮት ነበር (የሐዋ. 16፥6-8)። ምሁራን መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስ ወደዚህ አካባቢ እንዳያገለግል የከለከለው ጴጥሮስ ቀደም ሲል ወይም ወደ በኋላ በዚህ አካባቢ የወንጌል አገልግሎት ይሰጥ እንደነበረ ስለሚያውቅ ነው ይላሉ። ጴጥሮስ በእነዚህ ስፍራዎች ውስጥ መቼ እንዳገለገለ ባናውቅም፥ ብዙ ጊዜ እያገለገለ በመቆየቱ ምክንያት በአማኞች ዘንድ ሊታወቅ የቻለ ይመስላል። ጴጥሮስ በእነዚህ አካባቢዎች ስለነበሩት አማኞች አስገራሚ ገለጻ ያደርጋል። በመጀመሪያ፥ በእግዚአብሔር የተመረጡ ይላቸዋል። ጴጥሮስ ልክ እንደ ጳውሎስ እግዚአብሔር በምሕረቱ እያንዳንዱን አማኝ እንደ መረጠው ያውቅ ነበር። ድነትን (ደኅንነትን) አስመልክቶ የጴጥሮስ ትኩረት እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ያደረገው ተግባር እንጂ የእኛ ክርስቶስን መምረጥ አይደለም። ጴጥሮስ ይህንን የጻፈው በመከራ ውስጥ የሚያልፉትን ክርስቲያኖች ለማበረታታት ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከመረጣቸው፥ እያንዳንዳቸውን እንደ ውድ ልጆቹ ስለሚመለከት እንደሚጠብቃቸው ግልጽ ነው። ሁለተኛ መጻተኞች ይላቸዋል። ጴጥሮስ እነዚህ ስደት የበዛባቸው አማኞች ገና ከቤታቸው እንዳልደረሱ ያሳስባቸዋል። እንደ አብርሃም፥ በምድር ላይ በጉዞ ይኖሩ ነበር። እማኞች ወደ እውነተኛይቱ ቤታቸው የሚደርሱት መንግሥተ ሰማይ ሲደርሱ ብቻ ነው።

በመሆኑም፥ ከእምነታቸው የተነሣ ቤቶቻቸውንና ሥራቸውን በሚያጡበት ጊዜ ተስፋ ሊቆርጡ አይገባም። ምክንያቱም ማንም ከእነርሱ የማይወስደው ዘላለማዊ ቤት በሰማይ አላቸውና።

አንዳንድ ምሁራን ጴጥሮስ የአይሁዶች ሐዋርያ እንደ መሆኑ መጠን «የተበተኑ» የሚለውን ሐረግ እንደ ተጠቀመ ይናገራሉ። ይህም በሮም ግዛቶች ሁሉ ውስጥ የተበተኑትን አይሁዶች የሚያመለክት ቃል ነው። ጴጥሮስ መልእክቱን በቀዳሚነት የጻፈው በሰሜን ቱርክ የሚገኙ ጥቂት አይሁዳውያን አማኞች ለመሠረቷቸው አብያተ ክርስቲያናት ነበር። ነገር ግን የአንደኛ ጴጥሮስ መልእክት የተጻፈው በሰሜኑ የትንሹ እስያ ክፍል በተለያዩ ከተሞች ይሰበሰቡ ለነበሩ አይሁዳውያንና አሕዛብ አማኞች ይመስላል። በመሆኑም ይህ በስብሰባ ጊዜ በአንዱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከተነበበ በኋላ ወደ ሌላው ቤተ ክርስቲያን እየተላከ አብያተ ክርስቲያኑን በሞላ እንዲያዳርስ የታሰበ ተዘዋዋሪ ደብዳቤ ሳይሆን አይቀርም። እንዲያውም ጴጥሮስ የሮምን አውራጃ ዎች የጠቀሰበት ቅደም ተከተል መልእክቱን ለየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚያዳርሰው መልእክተኛ የሚሄድባቸውን ከተሞች ቅደም ተከተል የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ደብዳቤውን ገልብጠው ለራሳቸው ያስቀሩና ቀስ በቀስ እነዚሁ ቅጂዎች በክርስትናው ዓለም ውስጥ የተሰራጩ ይመስላል።

## አንደኛ ጴጥሮስ የተጻፈበት ጊዜና ስፍራ

ይህ መልእክት በትክክል መቼ እንደ ተጻፈ አናውቅም። በ95 ዓ.ም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጽሑፋቸው ውስጥ መልእክቱን ስለጠቀሱ፥ ከዚሁ ጊዜ ቀደም ብሎ እንደ ተጻፈ ለመረዳት ይቻላል። ጴጥሮስ በ68 ዓመተ ምሕረት በተጠናቀቀው የኔሮ ክርስቲያኖችን የማሳደድ ዘመቻ ውስጥ እንደ ሞተ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስለሚያመለክት፥ ይህ መልእክት ከዚሁ ጊዜ ቀደም ብሎ የተጻፈ ይመስላል። ይህ መልእክት ኔሮ ክርስቲያኖችን ማሳደድ ከጀመረ በኋላ ከ64-65 ዓመተ ምሕረት ባለው ጊዜ ውስጥ የተጻፈ ይመስላል። ጨካኙ ንጉስ ኔሮ የተባለው መሪ በተነሳበት ዘመን (54-68 ዓ.ም) ክርስቲያኖች በብዙ መከራና ስደት ውስጥ ያልፉ ነበር ። ሲጨልም ለመንገድ መብራት እሳት እንደሚሎከስ፣ ቅዱሳን በሕይወት እያሉ ታስረው በማቃጠል እንደ መብራት በየማዕዘናቱ ጥግ ይሰቀሉ ነበር ። ክርስቲያኖች ተሰደዋል፣ ተሰቃይተዋል፣ ተገድልዋል፤ ጳውሎስና ጴጥሮስም በዚህ በኔሮ ዘመን እንደ ሞቱ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል ።

ጴጥሮስ በመልእክቱ በመጨረሻ ላይ ከባቢሎን ለሆኑት አማኞች ሰላምታ ይልካል። በአዲስ ኪዳን ዘመን፥ የብሉይ ኪዳን ዘመኗ ባቢሎን ፈራርሳ ነበር። በዚህ ጊዜ ባቢሎን ተብላ ትታወቅ የነበረችው አነስተኛ መንደር ነበረች። ምንም እንኳን ጳውሎስ በዚህች አነስተኛ መንደር ውስጥ ሊኖር ቢችልም፥ የባቢሎንን ከተማ ማመልከቱ አልነበረም። በመጀመሪያው ምእተ ዓመት መጨረሻ ላይ አይሁዳውያንም ሆኑ ክርስቲያን ጸሐፊዎች የሮምን ከተማ ባቢሎን በሚባል ተምሳሌታዊ ስም ይጠሩ ነበር። ይህንንም ያደረጉት ቀደም ሲል ባቢሎን አይሁዶችን በምርኮኛነት ማጋዟን በማስታወስ አሁንም ሮም አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን እያሳደደች

መሆኗን በመገንዘባቸው ነበር። ስለሆነም፥ ጴጥሮስ ይህን መልእክት የጻፈው ከሮም ከተማ ይመስላል። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በኔሮ የስደት ጊዜ ጴጥሮስና ጳውሎስ በሮም ከተማ እንደ ነበሩና ጴጥሮስ መልእክቶቹን ከሮም ከተማ ሆኖ እንደ ጻፈው ያረጋግጣል።

## የ1ኛ ጴጥሮስ መልዕክት ዓላማ፣ ባሕሪያት፣ መዋቅር እና አስተዋጽኦ

የ1ኛ ጴጥሮስ መልእክት የተጻፈው ለተለያዩ ዓላማዎች ነበር

**የመጀመሪያው ዓላማ፡** አማኞች ምንም ዓይነት ስደት ወይም መከራ ቢደርስባቸው በእምነታቸው ጸንተው ይቆዩ ዘንድ ለማበረታታት (1ኛ ጴጥ 1፥6፤ 2፥20፣ 4፥13፥ 19) በክርስቲያኖች ላይ ስደት እየተጠናከረ መምጣቱን በመመልከቱ፥ ጴጥሮስ አዝማሚያው እየከፋ እንደሚሄድና ብዙ አማኞች ሕይወታቸውን እንደሚያጡ የተገነዘበ ይመስላል። ጴጥሮስ በስደቱ ከመረበሽ ይልቅ ክርስቲያኖች ስደትን የክርስትና ሕይወት አካላቸው አድርገው እንዲቀበሉትና ክርስቶስ እንዳደረገው እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ መከራ መቀበላቸውን መቀበልን እንዲማሩ ያበረታታቸዋል። እንዲያውም ጴጥሮስ እግዚአብሔር ልጆቹ በመንግሥተ ሰማይ ሽልማታቸውን ከመቀበላቸው በፊት በምድር ላይ መከራን እንዲጋፈጡ የሚፈቅድ መሆኑን ይናገራል። በዘመናችን ከጴጥሮስ የሚቃረን ትምህርት የሚያስተምሩ አንዳንድ አማኞች አሉ። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር መከራን እንድንቀበል (እንድንደኸይ፥ የምንወዳቸውን ሰዎች እንድናጣ፥ እና እንድንታመም) አይፈልግም ይላሉ። እነዚህ ነገሮች ከሰይጣን የሚመጡ በመሆናቸው፥ ሰይጣንን በመቃወም ልናሸንፋቸው እንደምንችል ያስተምራሉ። ወይም ደግሞ እነዚህ ችግሮች በሕይወታችን ውስጥ ኃጢአት ከመኖሩ የተነሣ የሚመጡ ናቸው ይላሉ። እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ እንደ መሆኑ መጠን ከእነዚህ ጊዜያት ይሰውረናል ብለው ያስተምራሉ። ነገር ግን አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያንና የብሉይ ኪዳን ታሪክ ጸሐፊዎች ይህ እውነት እንዳልሆነ ያስተምራሉ። እግዚአብሔር ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ መከራን እንዲቀበል እንደ ፈቀደ ሁሉ፥ ክርስቲያኖችም መከራን እንዲቀበሉ ይፈቅዳል።

**ሁለተኛ ዓላማ፡** አማኞች ከምድር ላይ ምቹና የተቃለለ ሕይወት ከመሻት ይልቅ ዓይኖቻቸውን በዘላለማዊ ቤታቸው ላይ እንዲተክሉ ለማበረታታት። ጴጥሮስ አማኞችን መጻተኞች ወይም ወደ ዘላለማዊ የመንግሥተ ሰማይ ቤታቸው እስኪደርሱ ድረስ በምድር ላይ የሚቅበዘበዙ ሰዎች አድርጎ ይገልጻል። ጳውሎስ ሰዎች ፈጥነው እንደሚጠወልግ አበባ መሆናቸውን ይናገራል (1ኛ ጴጥ 1፥24) ነገር ግን ክርስቲያኖች ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቃል ዘመን የማይሽረውን የመንግሥተ ሰማይ ርስት ተስፋ እንደሚገባልን መገንዘብ ይኖርብናል (1ኛ ጴጥ. 1፥3-6)

**ሦስተኛ ዓላማ፡** በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ለክርስቲያኖች ምክር ለመስጠት። ዋናው ነገር በሰላም ወደ መንግሥተ ሰማይ መድረስ ብቻ አይደለም። በዚህም ምድራዊ የእምነት ጉዞአችን የምንመላለስበት ሁኔታ ወሳኝ ነው። ስለሆነም ጴጥሮስ፥ ለባሎችና ሚስቶች (1ኛ ጴጥ 3፥1-7)፥ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች (1ኛ ጴጥ 5፥1-4)፥

እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚገኙ ወጣቶች (፲ኛ ጴጥ 5፥5) ምክሮችን ይሰጣል። በተለይም ጴጥሮስ ቅድስናና ትሕትና አስፈላጊዎች መሆናቸውን አጽንኦት ሰጥቶ ያስተምራል። ቅድስና እንድ ሰው ከኃጢአት ሕይወት ተመልሶ ለእግዚአብሔር ክብር መኖሩን ያሳያል። ትሕትና በዋናነት አማኞች እርስ በርሳቸው ምን ዓይነት ዝምድና ሊኖራቸው እንደሚገባና በተለይም ለሚያሳድዷቸው ሰዎች መልካም ባህሪ ማሳየት እንዳለባቸው ያሳያል።

## የ፲ኛ ጴጥሮስ መልዕክት ልዩ ባሕርያት

1. ጴጥሮስ ከክርስቶስ ጋር ከነበረው ግንኙነት የወሰዳቸውን ምሳሌዎች ይጠቀማል። ጴጥሮስ የሚለውን ስም የሰጠው ክርስቶስ ነበር። የስሙም ትርጓሜ ዓለት ማለት ነው። ነገር ግን ይህ ስም የተሰጠው ለእርሱ ብቻ አልነበረም። ክርስቲያኖች ሁሉ እግዚአብሔር እየገነባ ባለው መንፈሳዊ ቤት ውስጥ ሕያዋን ድንጋዮች ናቸው (፲ኛ ጴጥ. 2፥5-9)። ክርስቶስ በመጨረሻ አካባቢ ከጴጥሮስ ጋር ሲነጋገር በጎቼን አሠማራ ብሎት ነበር (ዮሐ 21፥15-18)። አሁን ግን ጴጥሮስ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን በጎች ሊንከባከቡ እንደሚገባ ያመለክታል (፲ኛ ጴጥ 2፥25፣ 5፥2፥ 4)።
2. ከመልእክቱ አጭርነት በተቃራኒ ጴጥሮስ ከብሉይ ኪዳን የወሰዳቸው ምንባቦች በየትኛውም የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ ከሚገኙ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች በልጠው ይገኛሉ። ጴጥሮስ የማይለወጥ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቃል ጠቃሚ በመሆኑ ላይ አጽንኦት ይሰጣል (፲ኛ ጴጥ 1፥23-25)።
3. ጴጥሮስ ክርስቲያኖች ለተወሰኑ ነገሮች መጠራታቸውን በመግለጽ፥ የክርስትናን ሕይወት ቁልፍ ነገሮች ይዘረዝራል (፲ኛ ጴጥ 1፥15፤ 2፥9፣ 3፥9፤ 5፥10) ጴጥሮስ በቅድስና፥ የእግዚአብሔርን ምስጋና ለማወጅ፥ ስደት የሚያመጡብንን ሰዎች ከመርገም ይልቅ ለመባረክ፥ እንዲሁም በሰማይ ወደሚጠብቀን ዘላለማዊ ክብር እስክንገባ ድረስ ለእምነታችን መከራ ለመቀበል የተዘጋጀን እንድንሆን ያብራራል።

## የ፲ኛ ጴጥሮስ መልዕክት መዋቅር

ብዙውን ጊዜ ጳውሎስ መልእክቶችን በሁለት ዐበይት ክፍሎች ይከፍላል። የመጀመሪያው ክፍል በዋናነት ስለ ነገረ መለኮታዊ እውነታችን ሲያስተምር፥ ሁለተኛው ክፍል የክርስቶስ ተከታዮች እንደ መሆናችን እንዴት መመላለስ እንዳለብን የሚያሳዩትን ተግባራዊ እውነቶች ያቀርባል። ጴጥሮስ ግን ሥነ መለኮታዊ እውነቶችን እግዚአብሔርን በሚያስከብርና የአማኞችን እምነት በሚያሳይ መልኩ መመላለስን ከሚያመለክቱ ተግባራዊ አንደምታዎች መካከል ይቀላቅላል።

በሁሉም ምዕራፍ ማለት ይቻላል እንደ ክርስቲያን መከራ የመቀበሉን ጉዳይ ያነሣል። የስደት ጭብጥ ደብዳቤው የተመሠረተበት አቋም ሆኖ እናገኘዋለን።

## የ1ኛ ጴጥሮስ መልእክት አስተዋጽኦ

1. መግቢያ (1ኛ ጴጥ 1፥1-2)
2. ድነታችን (ደኅንነታችን) ከመከራ ባሻገር ታላቅ ሽልማቶችን ያስገኛል (1ኛ ጴጥ 1፥3-12)
3. ድነት (ደኅንነት) ወደ ተቀደሰ ዓላማ ሊመራን ይችላል (1ኛ ጴጥ. 1፡13-2፡3)።
4. የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ በመንፈሳዊ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ሕያዋን ድንጋዮች ናቸው (1ኛ ጴጥ 2፥4-12)
5. የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ እንዴት ሊመላለስ ይገባል (1ኛ ጴጥ 2፥13-5፡11)

ሀ. አማኞች ለመንግሥት መሪዎች መገዛት አለባቸው (1ኛ ጴጥ 2፥13-17)

ለ. ክርስቲያን ባሪያዎች መከራ ሲደርስባቸውም እንኳን ለሰብአዊ ጌቶቻቸው መገዛት አለባቸው (1ኛ ጴጥ 2፥18-25)

ሐ. የእግዚአብሔር ሕዝብ ቤተሰባዊ ግንኙነቶች (1ኛ ጴጥ 3፥1-7)

1. ሚስቶች ለባሎቻቸው መገዛት አለባቸው (1ኛ ጴጥ 3፥1-6)
2. ባሎች ከሚስቶቻቸው ጋር በማስተዋል መኖር አለባቸው (1ኛ ጴጥ 3፥7)

መ. የእግዚአብሔር ሰዎች አላግባብ በሚሰደዱበት ጊዜ ሳይቀር ከሰዎች ሁሉ ጋር በሰላም መኖር አለባቸው (1ኛ ጴጥ 3፥8-22)

ሠ. አማኞች የተቀደሰ ሕይወት መምራት ይገባቸዋል (1ኛ ጴጥ 4፥1-6)

ረ. የእግዚአብሔር ሕዝብ ለሌሎች አማኞች ጥልቅ ፍቅር ሊኖራቸው ይገባል (1ኛ ጴጥ 4፥7-11)

ሰ. ክርስቲያኖች ስደትን በደስታ መቀበል አለባቸው (1ኛ ጴጥ 4፥12-19)

ሸ. በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ሊኖር የሚገባው ግንኙነት (1ኛ ጴጥ 5፥1-1)

6. ማጠቃለያ (1ኛ ጴጥ 5፥12-14)

## ጥናት አንድ፡ የክብር ተስፋ

<u>ከስደት ባሻገር ድነታችን (ደኅንነታችን) ትልቅ ሽልማት ያስገኝልናል</u>

**የንባብ ክፍል፡** 1ኛ ጴጥሮስ 1፡1-12

- **የውይይት ጥያቄ፡-** ሀ) ክርስቶስን ለመከተል በመወሰንህ/ሽ የደረሰብህ/ሽ ስደት መከራና ስቃይ አለ? ወይም ክርስቶስን ለመከተል በመወሰናቸው ከፍተኛ ሥቃይ የደረሰባቸውና በግል የምታውቃቸው ሰዎች ሁኔታ ምን እንደሚመስል ግለጽ። ለ) እንደነዚህ አይነት ሰው ወደ አንተ መጥቶ/መጥታ እግዚአብሔር ለምን በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ እንዲሰቃይ/እንድትሰቃይ እንደሚፈቅድ ቢጠይቅህ/ብትጠይቀህ፥ ምን መልስ ትሰጣለህ?

በመግቢያው ላይ፥ ጴጥሮስ የአማኞቹን ቀልብ ከእግዚአብሔር ጋር ወዳላቸው ግንኙነት ሲመልስ እንመለከተዋለን። ጴጥሮስ አማኞችን ምን ብሎ እንደሚጠራቸው እናያለን፡-

1. **የእግዚአብሔር ምርጦች፡**

   እግዚአብሔር አብርሃምን፥ ሙሴን ዳዊትንና ሌሎችንም ሰዎች እንደ መረጠ ሁሉ፥ እያንዳንዱ አማኝ የእርሱ ልጅ እንዲሆን መርጦታል። ዓለም ከንቱዎችና ሞኞች አድርጋ ብትቆጥረንም፥ በዓለም ውስጥ ካሉት ሰዎች ሁሉ መካከል እግዚአብሔር እንደ መረጠን ልናስታውስ ይገባል። እርሱ ከልቡ ይወደናል።

2. **መጻተኞች፡-**

   ስደት የሰውን ልብ ከሚያቆስልባቸው መንገዶች አንዱ ከምንፈልጋቸው ነገሮች የሚያራርቀን በመሆኑ ነው። ብዙውን ጊዜ ከቤተሰቦቻችን፥ ከዘመዶቻችን፥ ከማኅበረሰቡ፥ ወዘተ… ይለየናል። በዚህን ጊዜ ብቸኝነት ይሰማናል። ስደት አንዳንድ ጊዜም ከጥሩ አኗኗር፥ ከትምህርት፥ እንዲሁም ከሥራ ይለየናል። ጴጥሮስ ይህንን ብቸኝነት በመገንዘብ፥ ብቸኛ የሆንንበት እውነተኛ ምክንያት ገና ከቤታችን ስላልደረስን መሆኑን ይናገራል። ቤታችን በሰማይ ነው፡፡

3. **እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው፡**

   ጴጥሮስ እያንዳንዱ የሥላሴ አካል በደኅንነታችን ውስጥ እንዴት እንደ ተሳተፈ ያሳያል። እግዚአብሔር አብ ልጆቹ እንድንሆን መረጠን። የእግዚአብሔር ልጆች የሆንነው በአጋጣሚ ወይም በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ በመወለዳችን አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር አብ ከፍቅሩ የተነሣ እኛን መርጦ ልጆቹ አድርጎናል። ይህም የሚያስደንቅ ነገር ነው!

4. **በመንፈስ የመቀደስ ሥራ፡**

የእግዚአብሔርን ጥሪ እንድንሰማና እንድናምን የሚያደርገን መንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱ ይቀድሰናል ወይም ይለየናል። ይህም ማለት፡- ሀ) እኛን የእግዚአብሔር ልጆች ለማድረግ በዓለም ውስጥ ካሉት ሌሎች ሰዎች ይለየናል። ለ) በተቀደሰው አምላክ ፊት ቅዱሳንና ተቀባይነት ያለን ሰዎች ያደርገናል።

5. **ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ፡**

   እግዚአብሔር ያዳነን ከሲዖል እንድናመልጥ ብቻ አይደለም። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን በመታዘዝ እንድናስከብረው አድኖናል። የክርስቶስ ተከታዮች እንድንሆንና ለእግዚአብሔር እየታዘዝን እንድንኖር ነው። ብዙውን ጊዜ ይህ የታዛዥነት ጎዳና ወደ ስደት ይመራናል። ክርስቶስ ከሥቃዩ ባሻገር ለእርሱ ታማኞች ሆነን እንድንቀጥል ይጠይቀናል።

- **የውይይት ጥያቄ፡-** በስደት ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች እነዚህን አምስት እውነቶች ማወቃቸው አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?

ጴጥሮስ ለእነዚህ አማኞች ይህ ድነት (ደኅንነት) ምን ያህል ታላቅና ልዩ እንደሆነ ይናገራል። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለዚሁ ልዩ መዳን የተነበዩ ሲሆን ኤር. 31፥34 እግዚአብሔር ይህንን ተግባር ከፍጻሜ የሚያደስበትን ሁኔታ ለመረዳት ናፍቀው ነበር። እነዚህ ነቢያት ስለ ክርስቶስ ሞት በመተንበይ ለአዲሱ ኪዳን ዘመን አማኞች እያገለገሉ ነበር። ታላላቅ የሰማይ መላእክት እንኳን እግዚአብሔር ለኃጢአተኛ ሰዎች የሰጠውን ድነት (ደኅንነት) የሰጠውን ስጦታና የሰጠውን ፍቅር በመመልከት ተደንቀዋል።

- **የውይይት ጥያቄ፡** ነገር ግን እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ መከራ እንድንቀበል የሚፈቅደው ለምንድን ነው? ጴጥሮስ ልዩ ልዩ መከራ የሚላቸው ምን ምን ይመስልሃል/ሻል?

  መጽሐፍ ቅዱስ ለምን መከራ በሕይወታችን እንደሚመጣ ለማመልከት የሚያቀርባቸው አያሌ ምክንያቶች አሉ።

1. ጴጥሮስ እሳት ወርቅ እንደሚያጠራ ሁሉ መከራም ሕይወታችንን እንደሚያጠራ ይናገራል። መከራ እምነታችንን በማጥራት በሂደቱ ውስጥ እየበሰለ እንዲሄድ ያደርጋል። በተጨማሪም መከራ እግዚአብሔር ኩራትን፥ ራስ ወዳድነትን፥ የዓለምን ፍቅር፥ ወዘተ… በማቃጠል ባህሪያችንን ለመቅረጽ የሚጠቀምበት ዋና መሣሪያ ነው።
2. የእግዚአብሔር ልጆች በመከራ ጊዜ ጸንተው መቆማቸው እግዚአብሔርን ያስከብራል። እግዚአብሔርን ለሰጠን በረከቶች ሳይሆን ለማንነቱ ብለን እንደምናምን ማረጋገጣችን ነው።
3. መከራ ለእግዚአብሔር ፍቅር እንዳለን ያሳያል። እንደ ጴጥሮስ ክርስቶስን ባናየውም፥ እንወደዋለን፤ ከእርሱም ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለን። ነገሮች መልካም በማይሆኑበት ጊዜ ሳይቀር በክርስቶስ ያለንን እምነት ስንጠብቅ፥ ይኸው ፍቅር ይበልጥ እየጠራ ይሄዳል።

4. ጳውሎስ በመከራ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ለማገልገል እንድንችል እግዚአብሔር የሚጠቀምበት መሣሪያ እንደሆነ ገልጾአል 2ኛ ቆሮ 1፥3-7

- **የውይይት ጥያቄ፡** ሀ) አንድን መከራ የተጋፈጥክበትን ሁኔታ ግለጽ። ይህ መከራ ከላይ ከተጠቀሱት አራት ነገሮች ወይም ሌሎች ምክንያቶች በሕይወትህ ውስጥ የትኛውን የፈጸመ ይመስልሃል?

  ለ) ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ከወደደንና እምነት ካለን፥ መከራ፥ እንደማይደርስብን ይናገራሉ። ይህ እውነት ይመስልሃል? በአማኞች ላይ ስለሚደርስ መከራ ያለህን ግንዛቤ ለማስደገፍ የሚያግዙህ ጥቅሶች የትኞቹ ናቸው?

- **ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን?**

- **ማጠቃለያ፡** በዚህ ጥናት ውስጥ የተመለከትነው አማኞች በህይወታችን በተለያየ ስደት ውስጥ ስናልፍ ልናስተውል የሚገባን በክርስቶስ የተሰጠንን ቦታ በማወቅና በመጽናት የሚጠብቀንንየህይወት ተስፋ በመረዳት በእምነታችን በመጽናት ልንኖር ይገባናል።

- **የቃል ጥናት ጥቅስ፡** “በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ በክርስቶስ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ...” ኤፌ 1፥3

## ጥናት ሁለት፡ ቅድስና

ድነት (ደኅንነት) ወደ ተቀደሰ አኗኗር ሊመራን ይገባል

### የንባብ ክፍል (1ኛ ጴጥ. 1፡13-2፡3)

- **የውይይት ጥያቄ፡-** ሀ) ጴጥሮስ አማኞች እንዲያደርጉ የማይፈልጋቸውን አሉታዊ ነገሮች የዘረዘረው ለምን ይመስልሃል? ለ) በተለይ ስደትን ለሚጋፈጡ ክርስቲያኖች እነዚህ ነገሮች የሚያስፈልጉት ለምንድን ነው?

ብዙውን ጊዜ በመጀመሪያ የድነት (ደኅንነት) ተግባር ላይ አጽንኦት እንሰጣለን። አንድ ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ ደስ እንሰኛለን። በመሠረቱ ይህ ትክክለኛ እርምጃ ነው። ይህ ታላቅ መዳን በመሆኑ፥ ሰማያት ሁሉ ከእኛ ጋር ይደሰታሉ (ሉቃ 15፥7)

ነገር ግን ጴጥሮስ ድነት (ደኅንነት) ከዘላለማዊ ፍርድ ብቻ መዳን ሳይሆን፥ የአዲስ ሕይወት መነሻ እንደሆነ ይናገራል። አሁንም ጴጥሮስ በደኅንነታችን ታላቅነት ላይ ትኩረት ያደርጋል። ይህ እግዚአብሔር በልጁ እንዲጨክን ያደረገው ጉዳይ ነው። ውጤቱም ጊዜያዊ አይደለም። ሰዎች ሥጋዊ ፈውስ ማግኘታቸው እንደ ሣር መጠውለጋችውን (መሞታቸውን) አያስቀረውም። ድነት (ደኅንነት) ግን ዘላለማዊ በረከቶችን ያስገኛል። እግዚአብሔር በዘላለማዊ ቃሉ ይህን ስለተናገረ፥ አምነን ልንቀበለው ይገባል።

ጴጥሮስ ለእነዚህ በመከራ ውስጥ ላሉት ክርስቲያኖች አሁን እንደ እግዚአብሔር ልጆች የሚኖሩበት ሁኔታ እግዚአብሔርን የሚያሳስበው መሆኑን ይናገራል። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ፥ ልጆቹም እንደ እርሱ ቅዱስ እንዲሆኑ ይፈልጋል። ብዙውን ጊዜ ቅዱስ የሚለው ቃል ከኃጢአትና ከክፉ አኗኗር መነጠል እንደሆነ እናስባለን። በእርግጥ ይህ የቅድስና አካል ነው። ጴጥሮስ እንደ ሰው፥ ሌሎች ክርስቲያኖችን ወይም ስደት የሚያመጡብንን ሰዎች እንደ መጥላት፥ ማታለል ወይም ለራሳችን መጠቀሚያ ማድረግ፥ ግብዝነት (ለሌሎች መንፈሳዊ መስሎ ለመታየት መጣር)፥ ከእኛ በተሻለ ሁኔታ ላይ በሚገኙ ሰዎች መቅናት እንዲሁም ስለ ባህሪያቸውና ተግባራቸው ሐሰተኛ መረጃ በማሰራጨት ሰዎችን ማማት የመሳሰሉትን ሕይወቶች ማስወገድ አለብን።

ቅድስና ለእግዚአብሔር ክብር የመኖርን አዎንታዊ ገጽታን ያመለክታል። ጴጥሮስ ራስን መግዛት፥ ተስፋችንን በሰማይና እግዚአብሔር በሰጠን ሰማያዊ በረከት ላይ ማሳረፍ በዓለም ውስጥ የሰዎች መለያ ከሆነና ክፉ ምኞቶችን አለመከተል፥ የመጻተኝነት ሕይወት መምራት (ቤታችን በምድር ላይ ላፈራናቸው ተግባራት) ከእግዚአብሔር ፍርድን የምንቀበልበት ጊዜ እንዳለ ማወቅ፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መጠበቅ፥ ለሌሎች አማኞች እውነተኛ ፍቅር በማሳየት፥በመንፈሳዊ ብስለት ለማደግ መሻት ያሉትን ነገሮች ይጠቅሳል።

- **የውይይት ጥያቄ** ጴጥሮስ በአማኞች ሕይወት ውስጥ እንዲታዩ የሚፈልጋቸውን ነገሮች የዘረዘረው ለምንድን ነው? እነዚህ ነገሮች በተለይ በስደት ውስጥ ለሚያልፉ አማኞች የሚያስፈልጉት ለምንድን ነው?
    - **ማጠቃለያ**: መድኀኒታችንናን ጌታችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትን የሰጠን ከሞተ ሥራና ከዓመጽ ሥራችን በመቤዠት መልካምን ለማድረግ የሚቀና ሕዝብ ለራሱ መለየቱን እንመለከታለን። የተከፈለልንን ዋጋ አስተውለን በማወቅ በኑሮአችን እርሱን እንድናከብረው ይሁን።
    - **ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን?**
- **የቃል ጥናት ጥቅስ፡** *“ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደሆነ፥ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ።”* 1ኛ ጴጥ 1፥2

## ጥናት ሦስት፡ የንጉስ ካህናት

<u>የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ሕያዋን ድንጋዮች ናቸው</u>

**የንባብ ክፍል** (1ኛ ጴጥ 2፥4-12)

- **የውይይት ጥያቄ፡** ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን የመጠራታችን ዋና ዋና ዓላማዎች ምንድን ናቸው?

የአማኞች እውነተኛ ማንነት፡ ሀ) **ሕያዋን ድንጋዮች፡** ጴጥሮስ የአማኞችን እምነት ለመግለጽ የራሱን ስም ተጠቅሟል። የጴጥሮስ የመጀመሪያው ስም ስምዖን እንደ ነበር ታስታውሳለህ። ነገር ግን ክርስቶስ ከጴጥሮስ ጋር በተገናኘበት ወቅት የጴጥሮስን ስም ወደ ድንጋይነት ለወጠው። (በአረማይክ ኬፋ፥ በግሪክ ደግሞ ጴጥሮስ ሁለቱም ድንጋይ ወይም ዓለት የሚል ፍቺ ይሰጣሉ (ዮሐ. 1፥42) የእግዚአብሔር ቤት ከድንጋይና ከስሚንቶ የተሠራ ሕይወት የሌለው ሕንጻ ሳይሆን፥ ሕያው ቤት ነው። አንድ ሰው በሚያምንበት ጊዜ በዚህ ዘወትር እያደገ በሚሄደው በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ሕያው ድንጋይ ይሆናል።

ለ) **ቅዱስ ካህናት፡-** ክርስቲያኖች ባሪያዎች ወይም ጌቶች፥ የተማሩ ወይም ያልተማሩ፥ ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን እያንዳንዱ አማኝ ካህን ነው። ካህን እንደ መሆኑ መጠን እያንዳንዱ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር መሥዋዕቶችን የማቅረብ ዕድል አለው። ሰውነታችን (ሮሜ 12፥1-2) ገንዘባችን (ፊልጵ 4፥18) ምሥጋናችን (ዕብ 13፥15) እንዲሁም መልካም ተግባራችን (ዕብ 1፥16) ሁሉ ለእግዚአብሔር የምንሠዋው መሥዋዕቶቻችን ናቸው።

ሐ) **የተመረጠ ሕዝብ፡** በብሉይ ኪዳን የነበሩት አይሁዶች ከዓለም ሕዝብ ሁሉ ተመርጠው የእግዚአብሔር ልዩ ሕዝቦች (ዘጸ. 19፥5-6) ሆነዋል። ጠላቶቹ የነበርነውን ሰዎች የቤተሰቡ አባላት በማድረጉ እግዚአብሔር ታላቅ ምሕረቱን ገልጾአል።

መ) **የንጉሥ ካህናት፡** ጴጥሮስ ክርስቲያኖች እንደ ሌዊ ዝርያዎች ካህናት ብቻ ሳይሆኑ፥ እንደ ዳዊት ነገድ የንጉሥ ልጆች መሆናችንን ያስረዳል። ጴጥሮስ ክርስቲያኖች የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ልጆች በመሆናቸው ሊመኩ እንደሚችሉ ይናገራል። ይህ በምድር ላይ ለሰዎች፥ በግልጽ ሊታይ አይችልም።

ሠ) **እንግዶችና መጻተኞች፡** አሁን በምድር ላይ ጊዜያዊ ነዋሪዎች(ጎብኝዎች) የሆንን ያህል ልንመላለስ ይገባል። ሌሎች በክርስቶስ አምነው ይድኑ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጆች እንዴት እንደሚኖሩ ልናሳያቸው ይገባል።

- **የውይይት ጥያቄ፡** ለእግዚአብሔር የምናቀርባቸው መሥዋዕቶች ምን ምን ናቸው?

  - **ማጠቃለያ፡** እግዚአብሔር ግን ሰዎች የናቁትን ድንጋይ ወስዶ ክርስቶስን የአዲስ ሕዝብ ራስ አደረገው። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ ዓለም ሊጥለንና ከንቱዎች አድርጎ ሊቆጥረን ይችላል። እግዚአብሔር ግን ዓለም የናቀውን በመውሰድ ልዩ እና ዘላለማዊ የሆነው ሕንጻ አካል ያደርገናል። ሰዎች በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ቤት ውስጥ ምን ያህል አስፈላጊዎች እንደሆንን አያውቁም።

- **ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን?**

- **የቃል ጥናት ጥቅስ፡** “እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤” (1ኛ ጴጥ 2፥9)

**ጥናት አራት፡ ክርስትያናዊ ምሳሌነት**

<u>ለአለቆችና ለጌቶች መታዘዝ</u>

**የንባብ ክፍል፡** (፲ኛ ጴጥ 2፥13-25)

ባለፈው ጥናት አማኞች ለንጉስ ካህንነት የተመረጡበትን ጥሪ ዓላማና እና ይህን ድንቅ ጥሪ የሚመጥን ሕይወት እንዲመላለሱ አማኞች ከሕይወታቸው ማስወገድ ያለባቸውና ማድረግ የሚገባቸውን መንፈሳዊ ልምምዶች በዝርዝር ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ክርስቲያን በሚኖርበት ማኅበረሰብ ውስጥ ሊወክለው የሚገባው እግዚአብሔርን በመሆኑ ሕግ አክባሪ ፣ መልካም ሥነ ምግባር ያለውና ራሱን ከዓለም ርኩሰት ሊጠብቅ እንደሚገባው እንመለከታለን ።

- **የውይይት ጥያቄ፡-** ሀ) ክርስቲያኖች ለመንግሥት መሪዎች ሊገዙ የሚችሉባቸውን ምሳሌዎች ዘርዝር።

  ለ) ክርስቲያኖች ብዙውን ጊዜ መንግሥት የመሠረታቸውን ግዴታዎች ላለማሟላት ጥረት የሚያደርጉባቸውን መንገዶች ዘርዝር። እግዚአብሔር ይህንን አመለካከት እንዴት እንደሚመለከት ግለጽ።

ሀ. ክርስቲያኖች ለመንግሥት መሪዎች መገዛት አለባቸው (፲ኛ ጴጥ 2፥13-17) ሁሉም የመንግሥት ባለሥልጣናት እግዚአብሔርን ቢያከብሩም ባያከብሩም እግዚአብሔርን ቢያምኑም ባያምኑም፥ በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። ስለሆነም አማኞች መሪዎቻቸውን ማክበርና መታዘዝ ይኖርባቸዋል። ይህም ማለት ቀረጥን እንዲከፍሉ በሚጠየቁበት ጊዜ ከማጭበርበር ይልቅ መክፈል አለባቸው ማለት ነው። ወደ ማኅበራዊ ስብሰባዎች በመሄድ መሳተፍ አለባቸው ማለት ነው። ለከተማችንና ለሀገራችን ይበጀናል የምንላቸውን ሰዎች ለመመረጥ የሚያግዝ ድምጽ መስጠትንም ይጨምራል።

ለ. ክርስቲያን ባሪያዎች (ሠራተኞች) መከራ ቢቀበሉም እንኳን ለሰብአዊ ጌቶቻቸው መገዛት አለባቸው (፲ኛ ጴጥ. 2፡18-25)። ጌቶቻቸው (አሠሪዎቻቸው) መልካም፥ አፍቃሪ ወይም ሰው የሚጠሉ መሆናቸው ለውጥ አያመጣም። አማኞች ምንም ኃጢአት ሳይሠራ መከራ የተቀበለውን የክርስቶስን ምሳሌነት መከተል ይኖርብናል። ይህም በባህሪያችንና በተግባራችን ሁሉ ሊገለጥ የሚገባው ነው። ክርስቶስ ምንም ኃጢአት ሳይሠራ ለእኛ ኃጢአት ሲል ሞቷል። ከዚህም የተነሣ፥ ይቅርታ ተደርጎልን የክርስቶስን ጽድቅ ሰጥቶናል። በተመሳሳይ መንገድ ባሪያዎች (ሠራተኞች) ምንም ዓይነት ጥፋት ሳይፈጽሙ መከራ መቀበላቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። ክርስቲያን ባሪያዎች ለእምነታቸው ወይም ትክክለኛ የሆነውን ነገር በማድረጋቸው መከራን በሚቀበሉበት ጊዜ እንዴት የትሕትና መንፈስ ሊኖራቸው ይችላል? ጴጥሮስ ለዚህ ቁልፉ ለእግዚአብሔር ሥልጣን መገዛት እንደሆነ ይናገራል። እግዚአብሔር አንድ ቀን ፍትሕን ይሰጠዋል። ከሁሉም በላይ ክርስቶስ

ዛሬም እረኛችን በመሆኑ ነፍሳችንን ይጠብቃል። እንደ ባሪያዎች ስንሰደድ ወይም አለአግባብ ሥቃይ ሲደርስብን እርሱ ይታደገናል።

- **ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን?**
  - **ማጠቃለያ፡**- የክርስቲያን ሕይወት በየትኛውም አቅጣጫ ከዕንቅብ በታች እንደ ተቀመጠ ሻማ ለራስ ብቻ ከመሆን ያለፈ እና ብርሃኑ ደምቆ ለብዙዎች ጽድቅን በመግለጽ የሚያበቃ መሆን ይገባዋል።

- **የቃል ጥናት ጥቅስ፡** “ ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤” (1ኛ ጴጥ 2፥24)

## ጥናት አምስት፡ ክርስትና እና መከራ

<u>የእግዚአብሔር ሕዝብ ቤተሰባዊ ግንኙነት እና መልካም በማድረግ መከራን መቀበል</u>

**የንባብ ክፍል፡** (1ኛ ጴጥ 3፥1-22)

- **የውይይት ጥያቄ፡** የእግዚአብሔር ሕዝብ ቤተሰባዊ ግንኙነት ምን መምሰል አለበት?(1ኛ ጴጥ 3፥1-7)

እግዚአብሔር እንደሚፈልገን ለመኖር እና የሚደርስብንን ስደትና መከራ ለማሸነፍ የምንችለው ጤናማ ቤተሰባዊ ግንኙነት ካለን ብቻ ነው። ይህም ግንኙነት ከእግዚአብሔር አካል፥ ከወላጆች፥ ከልጆች፥ ከወንድሞችና ከእኅቶች ጋር የሚደረገውን ቤተሰባዊ ግንኙነት ይመለከታል።

1. ሚስቶች ለባሎቻቸው መገዛት አለባቸው (1ኛ ጴጥ 3፥1-6)። ጴጥሮስ ሚስቶች ለባሎቻቸው መገዛት እንዳለባቸው ያስተምራቸዋል። ባሎቻቸው ክርስቲያኖች ባይሆኑም እንኳን መታዘዝ አለባቸው፡፡ ሴቶች መንፈሳዊ ባሕርያትን እንዲያጎለብቱ ይመክራቸዋል። እግዚአብሔር ይህን መልካም ባህሪያቸውን በመጠቀም ባሎቻቸውን ወደ ክርስትና እምነት እንደሚያመጣ ያስተምራል።
2. ክርስቲያን ባሎች ደኅችና ከሚስቶቻቸው ጋር በማስተዋል አብረው የሚኖሩ መሆን አለባቸው (1ኛ ጴጥ 3፥7) ጴጥሮስ በዚህ ክፍል ውስጥ ሚስቶችን እንዴት እንደሚገልጽ እንመልከት።

ሀ) ተካፋዮች ናቸው፡፡ ሚስቶች ባሪያዎች አይደሉም። ወንድ እንደፈለገ የሚጫወትባቸው ንብረቶች አይደሉም። ይልቁንም ትዳሩን የመሠረተውን እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት አብረው በእኩልነት የሚሠሩ ተካፋዮች ናቸው።

ለ) ሚስቶች ከባሎቻቸው ጋር አብረው የሕይወትን ጸጋ የሚወርሱ ናቸው። ጴጥሮስ የሚናገረው ስለ ድነት (ደኅንነት) እና ዘላለማዊ በረከት ነው። እግዚአብሔር ወንዶችንና ሴቶች ልጆቹን የሚመለከተው በአንድ ዓይነት መንገድ ነው። እርሱ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ድነትን (ደኅንነትን) እና የዘላለም በረከቶችን እኩል እንዲወርሱ ያደርጋል።

ሐ) "ሴቶች ደካማ ፍጥረቶች ናቸው፡፡" ጴጥሮስ ይህንን ሲል ምን ማለቱ ነው? በሥነ ምግባርና በመንፈሳዊነት ከወንዶች ያነሱ ናቸው ማለቱ ይሆን? ምናልባትም ጴጥሮስ ሴቶች ደካማ ፍጥረቶች ናቸው ያለው ሁለት ነገሮችን ለማመልከት ይሆናል። ሴቶች በአካላዊ ጥንካሬ፣ የወንዶችን ያህል ብዙ ጭነት ሊሸከሙ ስለማይችሉ ነው እና ከሁሉም በላይ ሴቶች ከወንዶች ያነሰ ስሜታዊ ጥንካሬ ይታይባቸዋል።

- **የውይይት ጥያቄ፡–** ይህንን ቤተሰባዊ ግንኙነት ጤናማ አድርጎ መጠበቅ የሚያስፈልገውና በተለይም ባሎች ሚስቶቻቸውን መውደድ የሚያስፈልጋቸው ለምንድን ነው?
- **የውይይት ጥያቄ፡** መልካም በማድረግ መከራን መቀበል ሲባል ምን ማለት ነው? (1ኛ ጴጥ 3፥8-22)

ስደት ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ በሚመጣበት ጊዜ የተለያዩ ነገሮች ይፈትኗቸዋል። እነዚህን ፈተናዎች መቋቋሙ አስፈላጊ ነው። የሚጎዱንን ሰዎች የመጥላትና መበቀል ፈተና ይኖራል። ወይም ደግሞ የሚያሠቃዩንን ሰዎች ለመበቀል ፈተና ይሆንብናል። ከአለማውያን ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ላለማድረግ መፈተንም ይኖራል። ጴጥሮስ ክርስቲያኖች ለእነዚህ ፈተናዎች እጃቸውን እንዳይሰጡ ያስጠነቅቃል። ስደትን ከሚያመጡብን ዓለማውያን ጋር በሚኖረን ግንኙነት የሚከተሉትን ነገሮች ልናደርግ እንደሚገባ ይመክረናል፡

1. አማኞች ከጎረቤቶቻቸው ጋር በሰላም ለመኖር የሚችሉትን ጥረት ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል።
2. ክርስቲያኖች ለጎረቤቶቻቸው ትሕትናን፥ ርኅራኄንና ፍቅርን ማሳየት ይኖርባቸዋል።
3. የእግዚአብሔር ልጆች ጎረቤቶቻቸው በሚያሳድዱአቸው ጊዜ ሊበቀሏቸው፥ ወይም ሊሰድቧቸው አይገባም። ይልቁንም ክርስቲያኖች እርዳታ መጠየቅ የሚኖርባቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ ነው።
4. ክርስቲያኖች በልባቸው ክርስቶስን ሊቀድሱት ይገባል። ዓለም ከምትጠብቀው የተለየ ሕይወት ለመምራት መቁረጥ ይኖርብናል።
5. ክርስቲያኖች በእነርሱ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቋቸው ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጁ ሊሆኑ ይገባል።

- **የውይይት ጥያቄ፡-** ሀ) በአሁኑ ጊዜ ክርስቲያኖች ለስደት ምላሽ የሚሰጡት ጴጥሮስ ባስተማረው መንገድ ነውን? ለ) አንድ አማኝ በስደትና በመከራ በሰጠው መልካም ምላሽ ምክንያት እግዚአብሔር ብዙ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ያመጣበትን ሁኔታ ጥቀስ። ሐ) የአማኞች ትክክለኛ ያልሆነ ተግባርና አመለካከት ሰዎችን ከወንጌል ስላገለለበት ሁኔታ ምሳሌዎችን ስጥ።

ጴጥሮስ ክርስቶስ ከሞተ በኋላ የተከሰቱትን አንዳንድ ነገሮችን ጠቅለል አድርጎ ያቀርባል። ክርስቶስ ቢሞትም ተነሥቷል ክርስቶስ ከረጅም ጊዜ በፊት ላልታዘዙት መናፍስት በወኅኒ ሰብኮላቸዋል።

- **የውይይት ጥያቄ፡** ጴጥሮስ በኖኅ ዘመን የተፈጠረውን ሁኔታ ክርስቲያኖች ከሚያልፉበት ሁኔታ ጋር ያነጻጸረው ለምንድነው?"በወህኒ ቤት ለነበሩት ነፍሳት ሰበከላቸው" ይህ በኖኅ ዘመን ጋር ያለው ግ ንኙነት ምንድነው ብለህ/ሽ ታስባለህ/ቢያለሽ?

ለምሳሌ፥ የሐዋ 2፥38 ጴጥሮስ የውኃ ጥምቀት ድነትን ያስገኛል ማለቱ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ምክንያቱም ጥምቀት ከሰውነት ላይ እድፍን ማስወገድ ሳይሆን፥ ሕሊናን ማንጻት እንደሆነ ያስረዳል። ውኃ ኃጢአትን ሊያጥብ አይችልም። ይህን ሊያደርግ የሚችለው በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ ያለን እምነት ብቻ ነው።

- **የውይይት ጥያቄ፡-** ሀ) አንዳንድ ክርስቲያኖች ድነት (ደኅንነት) ከመጠመቅ እንደሚገኝ ሲያስተምሩ ሰምተህ ታውቃለህ? ለ) እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ወንጌል ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ስጦታ ሳይሆን ራሳችን የምናከናውነው ተግባር መሆኑን የሚያሳየው እንዴት ነው? ሐ) ጴጥሮስ ስለ ጥምቀትና ድነት (ደኅንነት) ያቀረበውን አሳብ እንዴት ትገልጻለህ?

- **ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን?**

  - **ማጠቃለያ፡** ክርስቶስ ነውርና ነቀፋ ያልተገኘበት ሆኖ ሳለ ስለ እኛ መከራን እንደቀበለ እኛም ከክርስትናችን የተነሳ በልዩ ልዩ በመከራ ውስጥ ልናልፍ እንችላለን። ይህን ስደትና መከራ ለማሸነፍ የምንችለው ጤናማ ቤተሰባዊ ግንኙነት ካለን ብቻ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

- **የቃል ጥናት ጥቅስ፡** "ክፉን በክፉ ፋንታ ወይም ስድብን በስድብ ፋንታ አትመልሱ በዚህ ፋንታ ባርኩ እንጂ በረከትን ልትወርስ ለዚህ ተጠርታችኋልና ።" (1ኛ ጴጥ 3÷9)

**ጥናት ስድስት፡ የተቀደሰ ሕይወት መምራት**

ለእግዚአብሔር መኖር እና ክርስቲያን በመሆን የሚደርስ መከራ

**የንባብ ክፍል፡** (1ኛ ጴጥ 4፥1-19)

- **የውይይት ጥያቄ፡** ክርስቲያኖች የተቀደሰ ሕይወት እንዴት መምራት ይኖርብናል ? (1ኛ ጴጥ 4፥1-6)

በመከራ ውስጥ በማለፍ ክርስቶስ ድልን ተቀዳጅቷል። እግዚአብሔር ክርስቶስን በማክበር ከሁሉም በላይ ሥልጣን ሰጥቶታል። ክርስቲያኖች መከራ በሚቀበሉበት ጊዜ የክርስቶስን ምሳሌነት ቢከተሉ ድል ነሺዎች ይሆናሉ። ብንሠቃይም፥ በኃጢአት ተፈጥሮአችን ላይ ድልን እንቀዳጃለን። መከራ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ላይ እንዲደገፉ ይረዳቸዋል። ከዘላለም ዘመን አንጻር አስፈላጊው ነገር ምን እንደሆነ ለይተው እንዲያውቁ ያግዛቸዋል። በሕይወታችን ውስጥ ያለውን ኃጢአት ተመልክተን እግዚአብሔርን ይቅርታ እንድንጠይቅ ያግዘናል። በስደት የሚሠቃዩት ሰዎች በአመዛኙ የዓለማውያንን ፈሪሃ እግዚአብሔር የጎደለበት ሕይወት አይጋሩም። ነገር ግን ክርስቲያኖች መከራ የሚያደርሱባቸው ሰዎች የሚቀጡበት ጊዜ እንደሚመጣ ማስታወስ ይኖርባቸዋል። በክርስቶስ ለሚያምኑ ክርስቲያኖች፥ የዘላለም ሕይወት ተዘጋጅቶላቸዋል። በክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች ግን የዘላለም ሞት ይጠብቃቸዋል። ጊዜያዊውን መከራ ተጋፍጦ ወደ ዘላለማዊ ሕይወት መሻገሩ አስተዋይነት ነው።

- **የውይይት ጥያቄ፡** አማኞች ከሌሎች አማኞች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ምን ይጠበቅባቸዋል ?(1ኛ ጴጥ 4፥7-11)

ጴጥሮስ ስለ ጸሎት በማካፈል ማብራሪያውን ይጀምራል። በሚያስገርም ሁኔታ እንደ ባለ አእምሮ ማሰብንና ራስን መቆጣጠርን ከጸሎት ጋር ያዛምደዋል። ጸሎታችን በራስ ወዳድነት ወይም በፍርሃት ላይ መመሥረት የለበትም። ይልቁንም ጸሎታችን አስፈላጊና ዘላለማዊ በሆኑት ነገሮች ላይ መመሥረት። መከራ በምንቀበልበት ጊዜ፥ «ይህን መከራ ከእኔ አስወግድ» የሚለው ጸሎት ወደ ልባችን መምጣቱ የማይቀር ነው። ነገር ግን ጴጥሮስ በመከራ ውስጥ የሚገለጹትን አንዳንድ የእግዚአብሔር ዓላማዎችንና ክርስቶስም በቅርብ ጊዜ እንደሚመለስ ከተረዳን ጸሎታችን እንደሚቀየር ይናገራል። በመከራችን ውስጥ ክርስቶስን ለማስከበር የምንችልበትን ኃይል እንድናገኝ መጸለይ እንጀምራለን፡፡ ለሚያሳድዱን ሰዎች ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት እንድንችል የእግዚአብሔርን ኃይል እንጠይቃለን። እግዚአብሔር ሕይወታችንን እንዲቀድሰው እንጠይቀዋለን። ደፍረን ለመመስከር እንድንችልም እንጸልያለን።

- **የውይይት ጥያቄ፡** በስደት ጊዜ ልናደርጋቸው ከሚገቡን ጉዳዮችን ምን ምን ናቸው?
- **የውይይት ጥያቄ፡** ክርስቲያኖች ስደትን በደስታ መቀበል አለባቸው? ለምን? (1ኛ ጴጥ 4፥12-19)
- **ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን?**

- **ማጠቃለያ፡** ክርስቲያኖች መከራን መቀበል ወይም መከራ የሚያደርሱባቸውን ሰዎች አለመበቀል ብቻ ሳይሆን፥ ስደትን እንደ ዕድል መቁጠር ደስ እንድንሰኝ ያደርገናል። ይህም በምንሰደድበትም ጊዜ ስለ እኛ መከራ ከተቀበለው ክርስቶስ ጋር እንተባበራለን። መሰደድ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ መኖሩን ያሳያል። ክርስቶስ በክብሩ በሚመለስበት ጊዜ ሽልማትን እንደምናገኝ እናውቃለን።

- **የቃል ጥናት ጥቅስ፡** “ስለዚህ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መከራን የሚቀበሉ፥ መልካምን እያደረጉ ነፍሳቸውን ለታመነ ፈጣሪ አደራ ይስጡ ።” (1ኛ ጴጥ 4፥19)

**ጥናት ሰባት፡ መልካም ምክር**

ለሁሉም የተሰጠ የማጠቃለያ ምክር

**የንባብ ክፍል፡** (1ኛ ጴጥ. 5፡1-14)

- **የውይይት ጥያቄ፡** የእግዚአብሔር ሕዝብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ዓይነት ግንኙነት ሊኖረው ይገባል? በተለይ በስደት ጊዜ የሽማግሌዎች ቀዳማይ ኃላፊነት ምንድን ነው?

ሽማግሌዎች የእግዚአብሔር መንጋ እረኞች እንደ መሆናቸው መጠን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን አማኞች ሁሉ በጥንቃቄ መጠበቅ ያስፈልጋቸዋል። ምንም እንኳን ይህ ተጨማሪ ሸክም ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ይህንን የአመራር ኃላፊነት ከሰጣቸው በደስታ ሊቀበሉት ይገባል።

- **የውይይት ጥያቄ፡** የቤተክርስትያን መሪዎች ሊገጥሟቸው የሚችሉ ተግዳሮቶች ምን ምን ናቸው?

ሽማግሌ የቤተ ክርስቲያን አባላት እረኛ ነው። ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያናቸውን አባላትን ሁሉ በግል ማወቅ ይኖርባቸዋል። ይህም አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፍሬያማ አገልግሎት እንዲያበረክቱ ለማበረታታትና ለማገዝ ያስችላቸዋል።

- **የውይይት ጥያቄ፡** ሀ. ብዙ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የማያድጉት፥ በሐሰት ትምህርት የሚወሰዱት ወይም ወደ ዓለም የሚመለሱት ለምን ይመስልሃል/ሻል? ለ. አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አባሎቻቸውን የሚያውቁና ፍላጎቶቻቸውን በበቂ ሁኔታ የሚያሟሉ ይመስልሃል? ካልሆነ፥ ለምን?

በመጀመሪያ አንድ ሰው ከሁኔታዎች ሁሉ ባሻገር ለእግዚአብሔርና ለሌሎችም መገዛት ይኖርበታል። የትሕትናን ትምህርት ሳይማሩ ወደ ሥልጣን ለመውጣት መቸኮሉ ለወጣቱ ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያኒቱም አደገኛ ነው። የሕይወትን ጠቃሚ ነገሮች ለመማርና ለመብሰል ጊዜን ይጠይቃል፡፡

- **የውይይት ጥያቄ፡-** ሀ) መሪዎች እግዚአብሔር የሚፈልገውን ዓይነት መሪ እንዳይሆኑ የሚከለክሏቸው ባሕርያት የትኞቹ ናቸው? ለ) ወጣቶች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን እርምጃዎች በትዕግሥት ለመቀበል ባለመቻላቸው ወደ መሪነት ሥልጣን ለመውጣትና ቅጽበታዊ ለውጥ ለማምጣት ሲጥሩ የተመለከትክበትን ሁኔታ አለ? ጴጥሮስ ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለውጥ ለማምጣት ስለሚሞክሩበት ሁኔታ ምን ምክር ሰጠ?

ጴጥሮስ ለአማኞች ሶስት ነገሮችን በአጽናኦት ያሳስባል 1. "እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃቸውን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት" አማኞችን የሚያስጨንቁ ብዙ ነገሮች አሉ። ከእነዚህም መካከል ስደት፥ የገንዘብ እጥረት፥ ሥራ አጥነት፥ በሽታና የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ። እግዚአብሔር እንደሚያስብልን በማመን፥ በጸሎትና በትሕትና ችግራችንን ለእርሱ ማሳወቅ ይኖርብናል። 2. "በመጠን ኑሩ ንቁም" ሁልጊዜም፥

በተለይም በመከራና በሥቃይ ጊዜ አማኞች ልባቸውንና ሕይወታቸውን በጥንቃቄ መጠበቅ ይኖርባቸዋል። መራርነትና ቁጣ እንዳይሞላን መጠንቀቅ አለብን። 3. "ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና፤ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት" ይላል።

- **የውይይት ጥያቄ፡** ክፉን እንዴት ነው የምንቃወመው?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰይጣንን ስለመቃወም የሚያሳየን ምሳሌ ክርስቶስ በምድረ በዳ ውስጥ የሰይጣንን ፈተና የተቃወመበት ነው (ማቴ. 4፥1-11) ክርስቶስ በቀዳሚነት የሰይጣንን ፈተና የተቃወመው የእግዚአብሔርን ቃል በመጥቀስ ነው። እንዲሁም ሰይጣን ከእርሱ ፈቀቅ እንዲል በማዘዝ ነው። የዚህ ትእዛዝ ዐውድ እንደሚያሳየው፥ በስደትና መከራ ጊዜ ሰይጣን በተለይ ተግቶ ይዋጋናል።

- **የውይይት ጥያቄ፡** ሰይጣን መከራ በምንቀበልበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የማይስማማ እርምጃ በመውሰድ በምንፈተንበት ጊዜም በሕይወታችን ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ መጣሩ የማይቀር ነው። በዚህ ጊዜ ምን ማድረግ ይኖርብናል? ድልንም የምንቀዳጀው እንዴት ነው?

1. መጸለይ አለብን፡- በክርስቶስ ኃይል ሰይጣን ከአካባቢያችን እንዲርቅ የማዘዝ ሥልጣን አለን? (መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ ስም መጸለይ ሲል ይህን ማለቱ ነው።)
2. በሕይወታችን ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ኃጢአት ማስወገድ አለብን። ንስሐ ያልተገባበት ኃጢአት የሰይጣን ምሽግ ነው።
3. እግዚአብሔር ከሰይጣን እንዲጠብቀን የእግዚአብሔርን የጦር መሣሪያ መታጠቅ አለብን። (ኤፌ 6፥10-18)
4. ክርስቶስ የእግዚአብሔርንም ቃል እንድንጠቀም ያስተምረናል። ሰይጣን በፈተነው ጊዜ ሁሉ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ቃል በመጥቀስ ነበር ምላሽ የሰጠው።
5. ጴጥሮስ የሰይጣንን ውሸቶች ላለማመን ቁርጥ ውሳኔ ማድረግ እንዳለብን ይነግረናል።

- **የውይይት ጥያቄ፡-** ሀ)ብዙ ክርስቲያኖች ሰይጣን ከአካባቢያቸው እንዲርቅ በተሟሟቀ ሁኔታ እየጸለዩ፥ ዳሩ ግን በግል ሕይወታቸው በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ በኃጢአት ላይ ድል የማይቀዳጁበትን ሁኔታ ለምን ይመስልሃል? ለ) እነዚህ ሰይጣንን የመቃወሚያ አምስት ነጥቦች አስፈላጊ ናቸው? ከሆነ በሕይወትህ ሰይጣንን ለመቃወም እንዴት እንደተጠቀምክባቸውና ሰይጣንን ከአካባቢህ እንዲርቅ እንዳደረገ ግለጽ?

የስንብት መልዕክት (1ኛ ጴጥ 5፥12-14) ጴጥሮስ ስልዋኖስ (ሲላስ) በዚህ ደብዳቤ ውስጥ አስተዋጽኦ እንዳደረገለት በመግለጽ መልእክቱን ይፈጽማል። ሲላስ እንዴት እንደረዳው አልተገለጸም። ምናልባት ደብዳቤውን ከጴጥሮስ ተቀብሎ ወደ ተከታዮቹ አድርሶ ይሆናል። ምናልባትም ደግሞ ሲላስ ጴጥሮስ

የሚናገረውን ቃል እየሰማ በጽሑፍ አስፍሮት ይሆናል። ጴጥሮስ በባቢሎን ካሉት ወገኖች ሰላምታ ያቀርባል። ጴጥሮስ ማርቆስን በስሙ ጠርቶታል። ቀደምት የቤተ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ማርቆስ በኋላ የጴጥሮስ ረዳት ሊሆን እንደቻለና ከጴጥሮስ ጋር ካለው ቅርበት የተነሣ የማርቆስን ወንጌል ሊጽፍ እንደበቃ ይናገራል።

- **ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን?**

    - **ማጢቃለያ፡** በጸሎት፥ ኃጢአትን በመናዘዝ፥ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ በመጠቀም፥ በቃሉ አማካኝነት፥ እንዲሁም ቁርጥ ውሳኔ በማድረግ፥ ሰይጣንን እናሸንፋለን። ንጹሕ ሕይወት ለመምራት ሳንቆርጥ መጸለይ ሰይጣንን አያሸንፈውም። ሳንጸልይ እና እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ሳንወስን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ብንጠቅስ ሰይጣን አይሸነፍልንም

- **የቃል ጥናት ጥቅስ፡** “ በክርስቶስ ላላችሁ ለሁላችሁ ሰላም ይሁን። አሜን” (1ኛ ጴጥ 5፥14)

**የ2ኛ ጴጥሮስ**

***መግቢያ***

ጴጥሮስ ሦስት ተኩል ዓመታት ከኢየሱስ ጋር አብሮ በመኖር፥ በመነጋገር፥ ሕይወቱን በመመልከት፥ በሞቱም በትንሣኤውና በእርገቱ በመደነቅ አሳልፎአል። ይህን መልእክት በሚጽፍበት ጊዜ ብዙ ዘመናት ስላለፉ እርጅና ተጫጭኖታል። እናም እስር ቤት ባይገባም ክርስቶስ በቅርቡ እንደሚሞት ነግሮታል። ጴጥሮስ እንደ ጻፈው፥ “ሁልጊዜም በዚህ ማደሪያ ሳለሁ በማሳሰቤ ላነቃችሁ የሚገባኝ ይመስለኛል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመለከተኝ ከዚህ ማደሪያዬ መለየቴ ፈጥኖ እንደሆነ አውቃለሁና” (2ኛ ጴጥ 1፥13-14) ብዙም ሳይቆይ ጴጥሮስ እንደ ጌታው በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞቷል። ከመሞቱ በፊት ግን ጴጥሮስ ክርስቲያኖች ጠቃሚ እውነቶችን እንዲያውቁ ፈለገ። ይህም ከክርስቶስ ጋር ባላቸው ሕይወት ማደግ እንዳለባቸው ነበር።

## የ2ኛ ጴጥሮስ ጸሐፊ

የሁለተኛ ጴጥሮስ ጸሐፊ ራሱን፥ “የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያና ሐዋርያ የሆነ ስምዖን ጴጥሮስ” ሲል ይገልጻል። ጸሐፊው ሐዋርያው ጴጥሮስ መሆኑ ክርስቶስ በተራራ ላይ መልኩን በለወጠ ጊዜ እንዳየው ከሚናገረው አሳብ ጋር ይጣጣማል (2ኛ ጴጥ. 1፥16-18፤ ማቴ. 17፥1-13) እንዲሁም ደግሞ ጴጥሮስ ይህ ሁለተኛ መልእክቱ እንደሆነ ይናገራል (2ኛ ጴጥ. 3፥1) ጸሐፊው በተጨማሪም፥ «የተወደደ ወንድማችን» (2ኛ ጴጥ 3፡15) ሲል የገለጸው ጳውሎስ በኖረበት ዘመን እንደኖረ ይናገራል። ይህ ሁሉ ማስረጃ የዚህ መልእክት ጸሐፊ ሐዋርያው ጴጥሮስ መሆኑን ያመለክታል።

በ1ኛ ጴጥሮስና 2ኛ ጴጥሮስ መልእክቶች መካከል ያለውን የመግቢያ ልዩነት መመልከቱ አስገራሚ ነው። በ2ኛ ጴጥሮስ፥ ጴጥሮስ ራሱን በሙሉ ስሙ ስምዖን ጴጥሮስ ሲል ይጠራዋል። ስምዖን አይሁዳዊ ስሙ ሲሆን፥ ጴጥሮስ ደግሞ የግሪክ ስሙ ነበር። ይህንንም ስም የሰጠው ደግሞ ክርስቶስ ነበር። በ1ኛ ጴጥሮስ፥ ሐዋርያ መሆኑን ሲያመለክት በ2ኛ ጴጥሮስ ደግሞ ባሪያ የሚለውን ቃል ያክላል።

## ጴጥሮስ መልእክቱን የጻፈው ለማን ነው?

ጴጥሮስ መልእክቱን ለማን እንደሚጽፍ ሲገልጽ፥ “በአምላካችንና በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ካገኘነው ጋር የተስተካከለ የክብር እምነት ላገኛችሁት” ይላል። ማለትም ለአማኞቹ ሁሉ ነበር። እነዚህ አማኞች እንደ ሰሜናዊ ትንሹ እስያ ባሉ የተወሰኑ አካባቢዎች የሚኖሩ አልነበሩም። ነገር ግን ይህ አጠቃላይ መልእክት በትንሹ እስያ ውስጥም ያሉትን አማኞች ያካትት ነበር። ምክንያቱም ጴጥሮስ ይህ ለእነርሱ የሚልከው ሁለተኛ መልእክት እንደሆነ ይናገራል። የመጀመሪያው መልእክት አንደኛ ጴጥሮስ ብለን የምንጠራው ነው (2ኛ ጴጥ. 3፡1) በዚህ አጭር መግቢያ ውስጥ ሁለት ጠቃሚ እውነቶችን ልንመለከት እንችላለን። በመጀመሪያ፥ ጴጥሮስ በአማኞች መካከል የደረጃ ልዩነቶችን ለመመልከት አልፈለገም እንዲሁም

ስለ ክርስቶስ አምላክነት ግልጽ የሆኑትን ትምህርቶች ይሰጣል፡፡ ጴጥሮስ ክርስቶስን አምላክና አዳኝ ሲል ይጠራዋል።

## 2ኛ ጴጥሮስ የተጻፈበት ጊዜና ቦታ

ጴጥሮስ የ2ኛ ጴጥሮስ መልእክትን በሚጽፍበት ጊዜ ገና እስር ቤት ውስጥ ባይገባም፥ ጴጥሮስ እንደሚሞት ያውቅ ነበር። ለዚህም ምክንያቱ ክርስቶስ በቅርቡ እንደሚሞት የገለጠለት መሆኑ ነው። 2ኛ ጴጥሮስ የተጻፈው ከ1ኛው የጴጥሮስ መልእክት በኋላ መሆኑ ግልጽ ነው (2ኛ ጴጥ. 3፡1)። ይሁንና፥ ከአንደኛው መልእክት በኋላ ሁለተኛው መልእክት ምን ያህል ዘግይቶ እንደ ተጻፈ አናውቅም። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያመለክተው፥ ጴጥሮስ በሰማዕትነት የሞተው በኔሮ የስደት ዘመን ነበር። ኔሮ የሞተው 68 ዓ.ም ስለነበረ ጴጥሮስ ይህን መልእክት ከዚያ ቀደም ብሎ መጻፉ የተረጋገጠ ነው። በተለይ መልእክቱ 65-68 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተጻፈ ይመስላል።

ጴጥሮስ ይህንን ደብዳቤ በጻፈበት ወቅት የት እንደነበረ በትክክል ለማወቅ አይቻልም። ምናልባትም ከሮም ከተማ ለሁሉም አማኞች፥ በተለይም በትንሹ እስያ ለሚገኙ ክርስቲያኖች የጻፈ ይመስላል።

### የ2ኛ ጴጥሮስ ዓላማ

የመጀመሪያው ዓላማ፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሐሰት ትምህርት በመስፋፋቱ ምክንያት ክርስቲያኖች በሐሰተኛ ትምህርቶች እንዳይወሰዱ ለማስጠንቀቅ ነው። ጴጥሮስ እንደሚለው፥ በመጨረሻው ዘመን ከሚከሰቱት ዐበይት ነገሮች አንዱ በፍጥነት የሚስራጩ ሐሰተኛ ትምህርቶች መኖራቸው ነው። ክርስቲያኖች እውነተኛ የሆነውንና ያልሆነውን እንዴት ለይተው ሊያውቁ እንደሚችሉ ግንዛቤ መስጠት ነው።

ሁለተኛ ዓላማ፡ ጴጥሮስ አማኞች በእምነታቸው ማደጋቸውን እንዲቀጥሉ በማበረታታት መዳን ብቻ በቂ እንዳልሆነና የእግዚአብሔር ዓላማ በባህሪ በመለወጥ እንድናድግና ውጤታማ የተቀደሰ ሕይወት እንድንኖር ለማስቻል ነው። ክርስቲያኖችን ከሐሰተኛ ትምህርት የምንጠበቀው በእውቀትና በመንፈሳዊ ባህሪ በማደግ፥ እንዲሁም በእምነታችን በመትጋት ነው።

ሶስተኛ ዓላማ፡ የእግዚአብሔር ቃልና የተስፋ ቃሎቹ ፍጹም እውነትና ልንደገፍ የምንችልባቸው መሆናቸውን ማወቅ።ክርስትያኖች መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ሐሰተኛ ትምህርቶችን ለመመርመር መጽሐፍ ቅዱስን ማውቁና መመሪያ ማድረጉ ጠቃሚ ነው።

አራተኛ ዓላማ፡ ክርስቶስ ተስፋ እንደገባው ለምን በፍጥነት አልተመለሰም? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ፡፡ በቶሎ እንደሚመለስ ተስፋ የሰጠው መዘግየቱ አንዳንድ ሰዎች ክርስቶስ የተናገረውን ስላልሆነ መጠራጠር ስለጀመሩ ነው። ጴጥሮስ ለዚህ ምላሽ በመስጠት፥ ሀ) የእግዚአብሔር የጊዜ አመለካከት ከሰዎች እንደሚለይ ያብራራል። ለእኛ ረጅም ጊዜ (ሺህ ዓመታት) ለእርሱ አጭር ነው (አንድ ቀን)። ለ) ክርስቶስ በፍጥነት ያልተመለሰበት ዋነኛው ምክንያት ብዙ ሰዎች ንስሐ ገብተው በክርስቶስ ለማመን ዕድል እንዲያገኙ ነው።

## የ2ኛ ጴጥሮስ ልዩ ባሕርያት

1. ብዙ ምሁራን የይሁዳን መልእክት ከ2ኛ ጴጥሮስ 2፥1-22 ጋር ያነጻጽራሉ። እንዲያውም ከይሁዳ መልእክት 25 ጥቅሶች መካከል 19ኙ ከ2ኛ ጴጥሮስ ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ይህ ማለት ጴጥሮስ የይሁዳን መልእክት ወይም ይሁዳ የ2ኛ ጴጥሮስን መልእክት ማንበቡን ወይም፥ ሁለቱም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተሰጠው አንድ ትምህርት በማጣቀሻነት መጠቀማቸውን ሊያመለክት ይችላል። ትክክለኛው ሁኔታ የትኛው እንደነበረ ግን ማወቁ አስቸጋሪ ነው። ሌላው አስተሳሰብ ጴጥሮስና ይሁዳ ሁለቱም ሌላ ሰው የጻፈውን ሰነድ በማጣቀሻነት ተጠቅመዋል የሚል ነው።
2. የዚህ መልእክት ቋንቋ የአጻጻፉ ስልት ከ1ኛ ጴጥሮስ የተለየ ነው። ይህም አንዳንድ ምሁራን ጴጥሮስ ይህን መልእክት አልጻፈው ይሆናል ብለው እንዲጠራጠሩ አድርጓቸዋል። ይሁንና ጴጥሮስ በ1ኛ ጴጥሮስ እንዳደረገው ሲላስን በጸሐፊነት ከመጠቀም ይልቅ እራሱ መልእክቱን እንደ ጻፈ ወይም ሌላ ጸሐፊ እንደ ተጠቀመ መገመት ይቻላል። የመልእክቶቹ ፍሬ አሳብ የተለያየ በመሆኑ የተለያየ የአጻጻፍ ስልት ተጠቅሞ ሊሆን ይችላል።
3. ጴጥሮስ የጳውሎስን መልእክቶች እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ይጠቅሳቸዋል (2ኛ ጴጥ. 3፥15-16)።

## የ2ኛ ጴጥሮስ መዋቅር

የ2ኛ ጴጥሮስ መልእክት የተዋቀረው በመጽሐፉ ውስጥ በሚገኙት ሦስት ዐበይት ትምህርቶች መሠረት ነው።

1. ጴጥሮስ ክርስቲያኖች በእምነታቸው እና በእግዚአብሔር ቃል እውቀት እንዲያድጉ ይመክራቸዋል (2ኛ ጴጥ. 1)። የመንፈሳዊ እድገት ቁልፍ ቁም ነገር ከመንፈስ ቅዱስ የሚመጣ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ነው።
2. ጴጥሮስ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ከሚበርዙ ሐሰተኛ ትምህርቶች እንዲጠበቁ ያስጠነቅቃል (2ኛ ጴጥ. 2)። እነዚህ አስተማሪዎች በትዕቢት፥ በራስ ወዳድነት እና ግብረገባዊነት በጎደላቸው አኗኗሮች የሚታወቁ ነበሩ።
3. ጴጥሮስ ክርስቶስ ተመልሶ አይመጣም የሚለውን ግምት በማፍረስ ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል (2ኛ ጴጥ. 3)። ጴጥሮስ ክርስቶስ ዳግም ተመልሶ እንደሚመጣና ዳሩ ግን እግዚአብሔር እንደ እኛ በጊዜ የተገደበ አምላክ አለመሆኑን ያስረዳል።

## የ2ኛ ጴጥሮስ አስተዋጽኦ

1. ጴጥሮስ አማኞች በእምነታቸውና በእግዚአብሔር ቃል እውቀት እንዲያድጉ ይመክራቸዋል (2ኛ ጴጥ 1)

ሀ) መግቢያ (2ኛ ጴጥ. 1፡1-2)

ለ) አማኞች በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት ለማረጋገጥ በመንፈሳዊ ባህሪ ማደግ አለባቸው 2ኛ ጴጥ 1፥3–11

ሐ) አማኞች ከመንፈስ ቅዱስ የመጣውን የእግዚአብሔርን ቃል እውነቶች ማስታወስ አለባቸው 2ኛ ጴጥ 1፥ 12-21

2. ጴጥሮስ አማኞች መጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ከሚበርዙ ሐሰተኛ አስተማሪዎች እንዲጠነቀቁ ያሳስባል 2ኛ ጴጥ 2
3. ጴጥሮስ ክርስቶስ እንደ ተስፋ ቃሉ አይመለስም የሚለውን አስተሳሰብ ያፈርሰዋል  2ኛ ጴጥ 3

## ጥናት አንድ፡ መመረጥና መጠራትን ማወቅ

<u>በእምነትና ስለ እግዚአብሔር ባለን እውቀት ማደግ</u>

**የንባብ ክፍል፡** (2ኛ ጴጥ 1፥1-11)

- **የውይይት ጥያቄ፡** 1. ለሞት ለማዘጋጀት በመጨረሻው ዓመት ላይ ብንሆን በምን ምን ጉዳዮች ላይ ትኩረት እናደርጋለን? 2. እግዚአብሔር እንዴት እንደ መረጠንና የመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች እንዳደረገን እናውቃለን?

እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ መቼ እንደምንሞት አይነግረንም። ነገር ግን እግዚአብሔር አንድ ቀን እንደምንሞት ያስጠነቅቀናል። ጴጥሮስ ይህን የ2ኛ ጴጥሮስ መልእክት የጻፈበት ዓላማ ክርስቲያኖች ዓለም ከምታብለጨልጭባቸው ጊዜያዊ ነገር ርቀው ዘላለማዊ በሆነው በእግዚአብሔር አጀንዳ ላይ እንዲያተኩሩ ለማበረታታት ነው። ጴጥሮስ ስለ ሞት በመጻፍ ፋንታ፥ የጌታ ቀን ላይ አጽንኦት በመስጥት"የጌታ ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል" አለ። የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት እየጠበቃችሁ እና እያስቸኮላችሁ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርን በመምሰል እንደምን ልትሆኑ ይገባችኋል"

- **የውይይት ጥያቄ፡** ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ተዘጋጅተሃል?ተዘጋጅተሻል?

ጴጥሮስን ያሳሰበው የመጀመሪያው ነገር በእውቀት እና በመንፈሳዊነት ማደግ መቀጠላቸው ነበር። አንድ ሰው በእውቀት ካላደገ በመንፈሳዊ ህይወት ሊያድግ አይችልም። ሰዎች በእውቀት ማደግ የሚያስፈልጋቸው በመንፈሳዊ ህይወት እንዲያድጉ ነው። ይህ እውነት በ2ኛ ጴጥሮስ የመጀመሪያው ክፍል ውስጥ ተመልክቷል። (2ኛ ጴጥ 1፥1-2) ጴጥሮስ መንፈሳዊ ልጆቹ በሕይወታቸው እንዲያድጉ መፈለጉን ገልጾአል። ስለ እግዚአብሔር ባለን እውቀት እና ከክርስቶስ ጋር ባለን ቅርበት እያደግን ስንሄድ በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ጸጋ እንለማመዳለን። በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥም ሳይቀር የእርሱ ሰላም አእምሯችንን ይሞላዋል። እማኞች በክርስቶስ ያለንን እምነት ለማረጋገጥ በመንፈሳዊ ባህሪ ማደግ ይኖርብናል 2ኛ ጴጥ. 1፡3-11 ድነት (ደኅንነት) የሚጀምረው በእውቀት ነው።

- **የውይይት ጥያቄ፡** የመንፈሳዊ ባህሪ መገጣጠሚያዎች እምነት፥ በጎነት፥ እውቀት፥ ራስን መግዛት፥ ጽናት፥ እግዚአብሔርን መምሰል፥ የወንድማማች መዋደድና ፍቅር ናቸው። የእግዚአብሔር ባህሪ በውስጣችን ስላለ እና የእርሱ ልጆች ስለሆንን፥ እነዚህ ነገሮች የባህሪያችን መገለጫዎች ሊሆኑ ይገባል ብለህ/ሽ ታስባለህ እንዴት? ለምንድነው እነዚህን እንድንጨምር የሚጠበቅብን?
- **ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን?**
    - **ማጠቃለያ፡** በክርስቶስ በኩል በእምነት ብቻ የጸደቅን ወይም የዳንን ብንሆንም መጠራታችንና መመረጣችን ደግሞ መልካሙን የእሱን ሥራ ለመሥራት እንደ ሆነ አውቀን

እንደዳነ ሰው እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቅብንን መንፈሳዊ ህይወትና ባሕርያትን ለመለማመድ ከበፊት ይልቅ ልንተጋ ይገባል ።

- **የቃል ጥናት ጥቅስ፡** “ስለዚህ ወንድሞች ሆይ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ ።” (2ኛ ጴጥ 1፥10)

## ጥናት ሁለት፡ የቅዱሳት መጽሃፍት ትንቢትን መመርመር

<u>ከመንፈስ ቅዱስ የሚመጡትን የእግዚአብሔር ቃል እውነቶችን ማወቅ</u>

**የንባብ ክፍል፡** (2ኛ ጴጥ 1፥12-21)

- **የውይይት ጥያቄ፡** በየጊዜው የተለያዩ ትምህርቶች ይመጣሉ፤ እውነት የሆነውን እና ያልሆነውን እንዴት ነው ማወቅ የምንችለው? እነዚህ ትምህርቶች ከእግዚአብሔር መሆናቸውን የምንገመግመው እንዴት ነው?

  ልክ እንደ ዛሬው ዘመን፥ የጴጥሮስ ዘመን የተፈጠሩ ተረቶች (ታሪኮች) ክርስቲያኖችን ግራ ያጋቡ ነበር። እነዚህ ትምህርቶች የተሳሳቱ ነበሩ፤ ጴጥሮስ ከእግዚአብሔር የሆኑትን ነገሮችና ከእግዚአብሔር ያልሆኑትን ለመለየት የሚቻልባቸውን ሁለት የመረጃ ምንጮች ይጠቁማል። በመጀመሪያ፥ የዓይን ምስክሮችን ይጠቅሳል። ጴጥሮስ ይህን ሲል እራሱን እና ሌሎች ሐዋርያትን ማመልከቱ ነበር። እራሱ ጴጥሮስ ክርስቶስ በተራራው ላይ ሲለወጥ ክብሩን እና ኃይሉን ለማየት በቅቷል። የእግዚአብሔር አብ ድምጽ ክርስቶስ ልጁ እንደሆነ ሲናገር ሰምቷል። እነዚህ ታሪኮች እና ትምህርቶች ዛሬ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ። እውነትን የምናውቀው ከእግዚአብሔር ቃል ነው። ሁለተኛ፥ የብሉይ ኪዳን ነቢያቶች መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ልብ ውስጥ ከመሥራቱ የተነሣ የተገኘ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

- **የውይይት ጥያቄ፡** ለእምነታችን ብቸኛ የሥልጣን መሠረት ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን መሆኑን አጥብቀን መገንዘብ ያለብን የማን የሥራ ውጤቶች በመሆናቸው ነው?

  እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን የእውነት መመዘኛ አድርጎ ሰጥቶናል። ሌሎች እምነቶች፥ ኃይማኖቶች እና ልምምዶች ሁሉ የሚገመገሙት በመጽሐፍ ቅዱስ ነው። ለአማኞች ሁሉ በተለይም ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተነገረውን መገንዘብ አስፈላጊ የሚሆነው ለዚህ ነው። ይህ ካልሆነ ለእውነት መሠረት አድርገን የምንወስደው፥ የምናስበውን፥ የሚሰማንን ስሜት፥ ከሰዎች የሰማነውን ወይም ቀደም ሲል ያከናወነውን ብቻ ይሆናል ማለት ነው።

- **የውይይት ጥያቄ፡** በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ምዕመኑ ሁሉ በቂ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጠና ማግኘታቸው አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? የእግዚአብሔር ቃል የህይወታችን መሰረት መሆኑን በመገንዘብ እንደክርስትያን በጨለማውስጥ እንደሚኖር ብርሃን ምን ያህል እንጠነቀቃለን?

- **ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን?**
  - **ማጠቃለያ፡** መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋሰ መለኮት /የእግዚአብሔር ንግግር/ መሆኑን በግልጽ ከሚናገሩ ምንባቦች ውስጥ አንዱ ይህ ክፍል ነው። ጴጥሮስ ቅዱሳት መጻሕፍት በሰው

ፈቃድ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት እንደ ተጻፉ ይናገራል። ይህ ደግሞ ማንም እነዚህን ቅዱሳት መጻሕፍት ለገዛ ፈቃድ ሊተረጉማቸውም ሆነ በዘፈቀደ እንዲጠቀምባቸው እንደማይችል ያስረዳል።

- **የቃል ጥናት ጥቅስ፡** “ትንቢት ከቶ በሰው ፍቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።” 2ኛ ጴጥ 1፥21

## ጥናት ሶስት፡ ሐሰተኛ ነብያትና አደገኛነታቸው

<u>መጽሐፍ ቅዱስን ከሚያዛቡ ሐሰተኛ አስተማሪዎች መጠበቅ</u>

**የንባብ ክፍል፡** (2ኛ ጴጥ 2፥1-22)

- **የውይይት ጥያቄ፡** ሐሰተኛ ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት ሊስፋፉ ይችላሉ? የገጠመህ/ሽ አለ?

አማኞች በእምነታቸው እና የእግዚአብሔርን ቃል በማወቅ የማያድጉ ከሆነ ለሃሰተኛ ትምህርትና አስተማሪዎች ይጋለጣሉ። የ2ኛ ጴጥሮስ መልእክት ዋነኛ ትምህርት ክርስቲያኖችን ስለ ሐሰተኛ ትምህርትና አስተማሪዎች ማስጠንቀቅ ነበር። በብሉይ ኪዳን ዘመን እውነተኛ ነቢያት በተነሣ ቁጥር ሐሰተኛ ነቢያትም ይነሡ ነበር። ከእግዚአብሔር እውነትን የሚናገሩ ሰዎች በሚነሡበት ጊዜ ውሸትን ከራሳቸው አመንጭተው የሚናገሩ ሰዎችም ብቅ ይሉ ነበር። የእነዚህም ሰዎች እሳብ ዋነኛው ምንጭ ሰይጣን ነው። ጴጥሮስ ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት ስተው ውሸትን በሚከተሉባት ጊዜ ምን እንደሚከሰት ታሪካዊ ምሳሌዎችን ይጠቅሳል። መላዕክት ኃጢአት በሠሩ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ወደ ገሃነም ጥሎ በጨለማ ጉድጓድ ለፍርድ ሊጠበቁ አሳልፎ ሰጥቷቸዋል። በመጨረሻው ፍርድ ሰይጣን እና መላእክቱ ሁሉ ፍርድን እስከሚቀበሉበት ጊዜ ድረስ ታስረው ይቆያሉ። እነዚህ መላእክት መቼ እንደ ወደቁ ባናውቅም፥ የተላለፈልን መልእክት ግልጽ ነው። ይኸውም በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ ታላቅ ቅጣትን እንደሚያመጣ ያስረዳል።

- **የውይይት ጥያቄ፡** የኖህንና ቤተሰቡን ምርጫ ስንመለከት ምን እንረዳለን? እንዲሁም ሰዶምና ገሞራ፤ ዛሬስ የምንመርጠውው እንደ ኖኅና ቤተሰቡ የጽድቅ ሕይወት ለመኖር እንመርጥ ይሆን? እንደ ሎጥና ሴቶች ልጆቹ እናመልጥ ይሆን ወይስ አብዛኛዎችን የጥፋት ሰለባዎች እንከተል ይሆን?

እንደ ኖህ ዘመን ዓይነት ዓለም ዓቀፍ የፍርድ ቀን ይመጣ ይሆናል። እነዚህ ምሳሌዎች እግዚአብሔር ጻድቃንና ለእርሱ በመታዘዝ የሚኖሩትን በዐመፅኛነት እንዳሻቸው ከሚኖሩት የሚለይ መሆኑን ያሳያል። እግዚአብሔር ጻድቃንን ከፍጻሜው ጥፋት ይታደጋቸዋል። ይህ ምናልባትም እግዚአብሔር በአሁኑ ዘመን በዓለም ላይ ከሚያመጣው ቅጣት መትረፍን ሊያመለክት ይችላል። እግዚአብሔር ሌሎች ከተጋፈጧቸው የመከራ ጊዜያት ልጆቹን እንደ ጠበቀ የሚያሳዩ ብዙ ምሳሌዎች አሉ። ነገር ግን ጴጥሮስ አጽንኦት የሰጠው ከዘላለማዊ ፍርድ እና ከሲዖል ስለ መዳን ነው።

- **ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን?**

  - **ማጠቃለያ፡** ጴጥሮስ ሊያስተላልፍ የፈለገው በረጅም ጊዜ ቆይታ ሐሰተኛ አስተማሪዎችን ከአኗኗራቸው ለይተን ልናውቅ እንደምንችል ነው። ለጊዜው መንፈሳዊያን መስለው ሊያሳስቱ ይችላሉ። ትምህርታቸውና ተግባራቸው ሊያስገርመን እና ሊማርከን ይችላል። የኋላ ኋላ ግን እውነተኛ ባህሪያቸው ይታያል። ሐሰተኛ አስተማሪዎች ብዙውን ጊዜ የኋላ ኋላ በሥልጣን፥

በገንዘብ ፍቅር ወይም በወሲብ ኃጢአት ይወድቃሉ። እነዚህንም ልናውቃቸውና ቶሎ ልንለይ ይገባናል።

- **የቃል ጥናት ጥቅስ፡** “እንግዲህ እንደ ጥበብኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ፤” ኤፌ 5፥15

## ጥናት አራት፡ የጌታን መምጣት መጠባበቅ

<u>ክርስቶስ ቃል እንደገባው ተመልሶ አይመጣም የሚል የሐሰተኞችን ትምህርት ማፍረስ</u>

**የንባብ ክፍል፡** (2ኛ ጴጥ 3፥1-18)

- **የውይይት ጥያቄ፡** ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረ አይመጣም የክርስቶስ መምጣት/ምጽአት/ የምባል ነገር የለም ይሚል አስተምህሮ ወይም ሰው ገጥሟችሁ ያውቃል? ምን ነበር ምላሻችሁ?

በአብያተ ቤተ ክርስቲያናት እየተሰራጩ ካሉት ሐሰተኛ ትምህርቶች የአንደኛውን አስተምህሮ ሲያፈርስ እንመለከታለን። የክርስቶስን ዳግም ምጽአት የተጠራጠሩ ሰዎች የነበሩ ይመስላል። “ሰዎች ሁልጊዜም ስለ ዓለም ፍጻሜ ሲተነብዩ ኖረዋል። ይሄ እስካሁን አልተከሰተም። ክርስቶስም በቶሎ እመለሳለሁ ብሎ ነበር። ነገር ግን ይኸው ከ30 ዓመታት በኋላም ብቅ አላለም። ይህም የክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚባል ነገር እንደሌለ ያሳያል” ይሉ ነበር። እንዲህ ዓይነት ነገር የሚናገሩ ሰዎች የጥፋት ውኃውን ትምህርት ዘንግተዋል። ይህ እግዚአብሔር ወደ ሰዎች ታሪክ በታላቅ ኃይል ገብቶ የማያምኑ ሰዎችን ያጠፋበትን ዘመን የሚያሳይ ነው። ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን የጊዜ ጽንሰ አሳብ አይረዱም። እግዚአብሔር እኛ በምንረዳው በጊዜ ቀመር ውስጥ የሚኖር አምላክ አይደለም

- **የውይይት ጥያቄ፡** ክርስቶስ ያልተመለሰበት ዋናው ምክንያት ምንድነው ብለህ?ሽ ታስባለህ/ሽ? ምንም ጊዜው ቢረዝም እንኳ ከእኛ የሚጠበቀው ምንድነው?

ጴጥሮስ፥ እነዚህ ሐሰተኞች የጳውሎስን መልእክቶች ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስን ሁሉ በተሳሳተ መንገድ እየተረጎሙ በማስተማር ላይ መሆናቸውን አስረድቷል። ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስ የብሉይ ኪዳን ነቢያትን በተጠቀመበት መንገድ ጳውሎስና ሌሎችን ሥልጣን ባለው መንገድ የተጠቀመ መሆኑን ተገንዝበው ነበር (2ኛ ጴጥ 1፥21) ዛሬ አብያተ ክርስቲያናችንን የሚያውኩት ሐሰተኛ አስተማሪዎች የተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ከዐውዳቸው ውጭ የትምህርታቸው መሠረት አድርገው ይጠቀማሉ። የእግዚአብሔርን ቃል በይበልጥ ባጠናንና የመጽሐፍ ቅዱስን ዓበይት ትምህርቶች ባወቅን መጠን፥ የሚመጡትን ትምህርቶች ሁሉ መርምረን እውነተኛውን ከሐሰተኛው ለመለየት እንችላለን።

- **የውይይት ጥያቄ፡** ሀ) ግንዛቤህና አስተምህሮህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዲሆን ምን እያደረግክ ነው? ለ) «መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት አያስፈልገኝም፥ መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛውንና ትክክለኛ ያልሆነውን ለይቼ እንዳውቅ፥ እንዲሁም ምን ማለት እንዳለብኝ ያስተምረኛል» ለሚሉ ሰዎች ምላሽ እንዴት ትሰጣለህ?

- **ከዚህ ክፍል ምን ቀረልን?**

  - **ማጠቃለያ፡** በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እያደኝ፥ የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናትና በመጠቀም፤ መጽሐፍ ቅዱስን አለአግባብ እየተጠቀሙ ከፊል እውነት የሚያስተምሩትን ሰዎች በጥንቃቄ በመምልከት በምንኖርበት ጊዜ፥ ራሳችንን በሐሰተኛ ትምህርት ከመወሰድ እንጠብቃለን። ለአዳነን ለኢየሱስ ክርስቶስ ስም ክብርን እናመጣለን።

- **የቃል ጥናት ጥቅስ፡** “ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ።” (2ኛ ጴጥ 3፥18)

**ዋቤ መጽሃፍት፡**

መደበኛ መጽሃፍ ቅዱስ 1962 እትም

አዲሱ መደበኛ ትርጉም 1993 እትም

### ድህረገጾች፡

ኤስ አይ ኤም የአዲስ ኪዳን መጽሃፍት ማጥኛ

ወንጌል በድህረ ገጽ ከመልዕክቶች ጥናት